በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት የውሃ ልማት ፈንድ ማመንጨትና ብድር አስተዳደርን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት

ጥር 2009 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ማውጫ

ማውጫ i

ማጠቃለያ (Executive summary) I

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የጽሕፈት ቤቱ አመሰራረት፡- 1

የጽሕፈት ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ 2

ራዕይ 2

ተልዕኮ 2

የጽሕፈት ቤቱ ዓላማ፣ ሥልጣን እና ተግባር 2

የጽሕፈት ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል 4

የጽሕፈት ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ 4

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ 6

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ 6

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Crieria) 6

ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ 7

የሥራ ፍሰት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION) 9

ክፍል ሁለት 10

የኦዲት ግኝቶች 10

2.1 የጽ/ቤቱ ፈንድ ማመንጨት ሂደት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን 10

በተመለከተ፤ 10

ጽ/ቤቱ ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት የፕሮጀክት ፕሮፖዛል /ፕሮፋይል/ ስለማዘጋጀቱ፣ 10

የጽ/ቤቱን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን ያስጠና መሆኑ በተመለከተ፣ 11

ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰበው ገንዘብ ምዝገባን በተመለከተ፤ 11

የፈንዱን ሂሣብ በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት መደረጉን በተመለከተ፣ 13

2.2 ጽ/ቤቱ የብድር አስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት 14

ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ፣ 14

ጽ/ቤቱ የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመርያ አዘጋጅቶ በቦርድ በማጸደቅ ብድር የሰጠ መሆኑን በተመለከተ፤ 14

በጽ/ቤቱ የብድር ተጠቃሚ ከተሞችን ለመምረጥ የሚያስችል የከተሞች መምረጫ መስፈርት ስለመኖሩ፣ 15

ከተበዳሪ ተቋማት የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ (Matching Fund) በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ፡፡ 16

ከተበዳሪዎች መሰብሰብ የሚገባውን የብድር ተመላሽና ወለድ በወጣው መርሀ ግብር መሠረት የተሰበሰበ መሆኑንና በወቅቱ ያልተሰበሰበ ብድር ሲኖር እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፤ 18

ብድር ለመጠየቅ ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የአዋጭነት ጥናቶችና ዲዛይኖች ተግባራዊ መሆናቸውን በተመለከተ፤ 20

ብድር ፈላጊዎች ወቅታዊ Business Plan, Feasibility study and Detail desig እንዲሁም ዋስትና ያቀረቡ መሆኑን በተመለከተ፣ 22

በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን የክትትል እና የግምገማ ሥራዎች በተመለከተ፣ 24

ጽ/ቤቱ ባስቀመጠው ያገልግሎት ስታንዳርድ መሠረት ብድር እየሰጠ ስለመሆኑ፣ 25

2.3 ጽሕፈት ቤቱ ከፈጻሚ ባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋና ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ 26

የጽ/ቤቱ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ 26

ጽ/ቤቱ ስለሚያከናውናቸው ሥራዎች ለተበዳሪዎች እና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ የሰራ ስለመሆኑ፣ 27

የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ ዘመናዊ በሆነ የመረጃ ቴክኖሎጂ ተደግፎ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ፤ 27

የጽ/ቤቱን የተለያዩ መረጃዎች ለባለድርሻ አካላትና ተጠቃሚዎች ለማድረስ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ስለመኖሩ፣ 28

የጽ/ቤቱን ስራ በተመለከተ ከተገልጋዮች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ ስለመኖሩ፣ 29

ክፍል ሶስት 31

መደምደሚያ 31

ክፍል አራት 34

የማሻሻያ ሃሳቦች 34

አባሪ 1፡ የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት ድርጅታዊ መዋቅር 37

አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) 38

አባሪ 3፡ በናሙና የታዩ ባለድርሻ አካላት እና የውሃና ፍሳሽ 41
አገልግሎት ተቋማት 41
አባሪ 4፡ ከፋይናንስ ሥራ ሂደት 14/11/2008 እና 25/11/2008 42
ዓ.ም የተሰጠ ሪፖርት ላይ የፕሮጀክት መዋጮ የተሰብሳቢ ሂሳብ የአመዘጋገብ ልዩነት 42
አባሪ 5 ፡ፕሮጀክታቸው ተጠናቀው ያልተሰበሰበ የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ...43
አባሪ 6፡ የብድር ተመላሽ በወቅቱ ያልመለሱ የከተሞች ውሃና.................................44
ፍሳሽ አገልግሎት ተቋም...44
አባሪ 7፡ የብድር ዋስትና የገቡበት ማስረጃ ያልቀረበ ከተሞች..................................45
ዝርዝር..45

ማጠቃለያ (Executive summary)

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 ዓ.ም በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ኦዲቱ ፈንድ ማመንጨትና ብድር አስተዳደር ውጤታማና አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ ላይ የተከናወነ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው የአራት በጀት ዓመታትን ከ2005- 2008 ዓ.ም እና የ2009 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን በማካተት ነው፡፡

ለሕብረተሰቡ አስተማማኝና ዘለቄታዊነት ያለው የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል የውሃ አቅርቦትንና ሳኒቴሽን አገልግሎት ለማጠናከር እና በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ የመስኖ እርሻ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጠው ተግባራት አንዱ በመሆኑ፤ እነዚህንም አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊውን ገንዘብ ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብ ፍትኃዊና ርዕታዊ በሆነ መንገድ ጠቃሚ የሚሆንበትን አሰራር በመቀየስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት ጥር 23 ቀን 1994 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 268/1994 እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

በመሆኑም ውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ሊፈጽማቸው ሲገባ ያልፈጸማቸው ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ጽ/ቤቱ በዜጎች ቻርተሩ መሰረት ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት የፕሮጀክት ፕሮፋይል አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያላቀረበና ለዚህ አገልግሎት የሚሆን ፋይናንስ የማፈላለግ ሥራ ያልሰራ መሆኑ፤
- የጽ/ቤቱን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን ያላስጠና መሆኑ፤
- ጽ/ቤቱ ከተለያዩ ምንጮች ለፈንዱ የሚሰበስበውን ገንዘብ ትክክለኛ እና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብትን ከደጋፊ ሰነዶች ጋር በመያዝ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ በወቅቱ በትክክል የማይመዘገብ እና የፈንዱን ሂሣብ በወቅቱ የማይዘጋ በሆኑ፣
- ጽ/ቤቱ የፈንዱን ሂሣብ በየአመቱ በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት ማስደረግ ያለበት ቢሆንም የፈንዱ ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ መሆኑ፤
- ጽ/ቤቱ ብድር ለመስጠት የሚያገለግል ረቂቅ መመሪያ ቢያዘጋጅም ለሚመለከተው አካል አቅርቦ እንዲጸድቅ ያልተደረገ በመሆኑ በየአመቱ የሚሰጠው ብድር ግልጽ እና ተጠያቂነትን የማያሳይ መሆኑ፣

- ጽህፈት ቤቱ ለብድር ተጠቃሚ ከተሞች መምረጫ የሚያገለግል መመሪያ ወይም የመመረጫ መስፈርት ያላዘጋጀ መሆኑ፤
- ጽ/ቤቱ ለሁሉም ተበዳሪዎች ለሚሰበስበው የፕሮጀክት መዋጮ (Matching Fund) የብድሩን መጠን ስንት መቶኛ(ፐርሰንት) ማዋጣት እንደሚገባቸው የሚወስን ግልጽ መስፈርት ያልተዘጋጀ መሆኑ እና ተበዳሪ ተቋማት የፕሮጀክት መዋጮ እንዲያዋጡ የማይደረግና ማዋጣት ከጀመሩትም በወቅቱ የማይሰበስብ መሆኑ፤
- ከጽ/ቤቱ ቅድሚያ ብድር አግኝተው ከተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ውስጥ ያልተሰበሰበ የብድር ተመላሽና ወለድ በድምሩ ብር 111,954,101.70 (አንድ መቶ አስራ አንድ ሚልዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሣ አራት ሺህ አንድ መቶ አንድ ብር ከሰባ ሳንቲም) ያልሰበሰበ መሆኑ፤እና፡-
- ለቆጋ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ 37.84 ሚልዮን ዩሮ ወጪ የወጣ ቢሆንም በወቅቱ ያልተሰበሰበ መሆኑን፣
- ጽ/ቤቱ ከከተሞች ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ጋር በገባው የብድር ውል ስምምነት መሰረት በወቅቱ ብድር በማይከፍሉ ተበዳሪ ከተሞች ላይ በብድር ውሉ መሰረት የተጨማሪ የወለድ ወለድ ቅጣት መክፈል እንዳለባቸው በውሉ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም ጽ/ቤቱ የማያስከፍል መሆኑ
- ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎች በቅድሚያ የጥናት ሰነዶቹ የተሟሉና ወቅታዊ ስለመሆናቸው እንዲሁም ከክልል መቅረብ ያለበት ዋስትና መቅረቡን የማያረጋግጥ መሆኑ፣
- ጽ/ቤቱ በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እየተከናወኑ እና ለታለመላቸው ዓላማ እየዋሉ ስለመሆኑ የክትትል እና የግምገማ ሥራዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ የማይከናወን መሆኑ፤
- የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ ዘመናዊ በሆነና በተጠናከረ የመረጃ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ አስተማማኝና የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲሰትጥ ያላደረገ መሆኑ፤
- ጽ/ቤቱ ወጪን ማስመለስ መርሆ እና የተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀምን በተመለከተ ለተበዳሪዎች እና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ያልሰጠ መሆኑ፤
- የጽ/ቤቱን ሥራ በተመለከተ ከተገልጋዮች፣ ከአስፈጻሚዎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በየዓመቱ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በብድር አቅርቦት፣ አፈጻጸማቸው እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ውይይት የማያደርግ መሆኑ፡፡

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ የተመለከቱት ግኝቶች መፍትሄ የማያገኙ ከሆነ የአገሪቱ ብድር ፈላጊ ተቋማት ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡ እንዲሆኑ ይህ ደግሞ ለሕብረተሰቡ አስተማማኝና ዘለቄታዊነት ያለው የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን አገልግሎትና በምግብ ራስን ለመቻል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግ መሆኑን በኦዲቱ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ጽ/ቤቱ ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት ፕሮጀክት ወጭን በማስመለስ መርሆ ላይ የተመሰረተ የረዥም ጊዜ ብድር ለመስጠት እንዲችል የፕሮጀክት ፕሮፋይል አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብና ክትትል በማድረግ ፋይናንስ ሊያፈላልግ ይገባል፡፡
- የጽ/ቤቱን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በማጥናት/በማስጠናት ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል
- ጽ/ቤቱ ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስበውን ገንዘብ የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መመርያ ቁጥር 5/2003 አንቀፅ 9 ገፅ 15 መሰረት በወቅቱ ተከታትሎ ሊመዘግብና ሂሣቡን በወቅቱ ሊዘጋ ይገባል፡፡
- ጽ/ቤቱ የፈንዱን ሂሳብ በያመቱ ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሪፖርቶች ለቦርዱ እንዲቀርቡ ማድረግ አለበት፡፡ በቀረቡት ሪፖርቶች መሰረትም ተገቢ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ መደረግ አለበት፡፡
- ጽ/ቤቱ በአዋጅ 268/1994 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነደደው መሰረት የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛ መመሪያ በማዘጋጀት (የተዘጋጀውን ረቂቅ የብድር አሰጣጥ መመዘኛ በማጠናቀቅ) በቦርድ አጸድቆ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
- ጽ/ቤ የብድር ተጠቃሚ ለሚሆኑ ከተሞችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ የከተሞች መምረጫ መስፈርት መመርያ ሊኖረው ይገባል፡፡
- በጽ/ቤቱ ከሁሉም ተበዳሪዎች ለሚሰበስበው የፕሮጀክት መዋጮ (Matching Fund) የብድሩን መጠን ስንት መቶኛ(ፐርሰንት) ማዋጣት እንደሚገባቸው የሚወስን ግልጽ መስፈርት በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ በማድረግ ሊያስከፍልና በቅቱ ሊሰበስብ ይገባል፡፡ በተጨማሪም በአዋጁ 581/2000 አንቀፅ 6 መሰረት በብድር ውላቸውና በመርሀ-ግብሩ መሰረት ከተበዳሪዎች ተመላሽ ሊደረግ

የሚገባውን የብድር ተመላሽና ወለድ በወቅቱ ሊሰበሰብና መልሶ ለሌሎች ተበዳሪ ተቋማት ሊያበድር ይገባል፡፡

- ተበዳሪ ተቋማት የወሰዱትን ብድር በወቅቱ የማይከፈሉ ከሆነ ጽ/ቤቱ በውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎች በቅድሚያ የጥናት ሰነዶቹ ወቅታዊና አዋጭ መሆናቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ስለዚህ ጽ/ቤቱ ለብድር ፈላጊዎች ብድር ከመስጠቱ በፊት ወቅታዊ የቢዝነስ ዕቅድ፣ የአዋጭነት ጥናት እና ዝርዝር የዲዛይን ጥናት (Business Plan, Feasibility study and Detail desig) እንዲሁም የክልል ዋስትና ሰነዶች ተሟልተው የቀረቡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ጽ/ቤቱ በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ተጀምረው ርክክብ እስከሚደረግላቸው ጊዜ ድረስ በታቀደላቸው ጊዜና ገንዘብ እንዲያልቁ እና ለታለመላቸው ዓላማ የዋሉ ስለመሆናቸው እቅድ በመያዝ የክትትልና የግምገማ ሥራዎች ሊሰራ ይገባል፡፡
- የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ ዘመናዊ በሆነና በተጠናከረ የመረጃ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ አስተማማኝና የተቀላጠፈ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡
- የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ ዘመናዊ በሆነና በተጠናከረ የመረጃ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ አስተማማኝና የተቀላጠፈ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡
- ጽ/ቤቱ ወጪን ማስመለስ መርሆ እና የተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀምን በተመለከተ ለተበዳሪዎች እና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ ይገባል፤
- የጽ/ቤቱን ስራ በተመለከተ ከተገልጋዮች፣ ከአስፈጻሚዎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በየዓመቱ የውይይት መድረክ ሊያዘጋጅና በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. መንግስት ማህበራዊ አገልግሎቶችን እና መሠረታዊ ልማቶችን ለሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች በእኩልነት ለማዳረስና አገልግሎቱን በማስፋፋት የተጠናከረ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ ከእነዚህም መሠረታዊ ልማቶች መካከል ዋነኛውና ተቀዳሚው የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ሳኒቴሽን አገልግሎት እና የመስኖ ልማት አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት በአሁኑ ወቅት ለንጹህ መጠጥ ውሃ፣ ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት ትኩረት በመስጠት የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ በማውጣት በቂ፣ አስተማማኝና ንፁህ የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን አገልግሎት በማሟላት የህዝቡን ጤንነትና ምርታማነትን ማጎልበትና የእንስሳት፣ የኢንዱስትሪን እንዲሁም የሌሎች የውሃ አቅርቦት ተጠቃሚዎች ፍላጎትን በማሟላት ለክፍለ ኢኮኖሚው የሚኖረውን ተጨባጭ ሁኔታ አስተዋፅኦ ማጎልበት እንደሆነ በማመን እና ቀልጣፋ፣ ተስማሚ እና ዘላቂነት ያለው የመስኖ ልማት አቅርቦት በጥራት በመሸፈን እየሰራ ይገኛል፡፡
2. በመሆኑም የሀገሪቱ የውሃ ሃብት በአግባቡ ለምቶ ለፈጣን እና ዘላቂ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገት የላቀ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት በማድረግ በከተሞችና በገጠሩ ክፍል የህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተዳምሮ የንፁህ መጠጥ ዉሃ፣ ሳኒቴሽን እና የመስኖ ልማት ተግባራዊ ለማድረግ ገንዘብ ከተለያዩ ምንጮች በማዕከል በማሰባሰብ ለሁሉም አቅርቦቱን በተሻለ ሁኔታ ተደራሽ ለማድረግ የውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤትን በአዋጅ 268/1994 እንዲቋቋም አድርጓል፡፡

የጽሕፈት ቤቱ አመሰራረት፡-

3. ለሕብረተሰቡ አስተማማኝና ዘለቄታዊነት ያለው የውሃ አቅርቦትና ሳኒቴሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል የውሃ አቅርቦትንና ሳኒቴሽን አገልግሎት ለማጠናከር እና በምግብ ራስን ለመቻል በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ የመስኖ እርሻ ልማት ከፍተኛ ትኩረት ከሚሰጠው ተግባራት አንዱ በመሆኑ፤ እነዚህንም አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊውን ገንዘብ ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብ ፍትኃዊና ርዕታዊ በሆነ መንገድ ጠቃሚ የሚሆንበትን አሰራር በመቀየስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የውሃ ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት ጥር 23 ቀን 1994 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 268/1994 ተቋቁሟል፡፡

4. በመቀጠልም የውሃ ልማት ፈንድን ለማቋቋምና አስተዳደሩን ለመወሰን የወጣ /ማሻሻያ/ አዋጅ በሚል እንደገና በአዋጅ 581/2000 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣ ሲሆን፤ ይህም ብድር በመስጠትና ብድሩን በወቅቱ ሰብስቦ ለተመሣሣይ የልማት ስራዎች ማስፈፀሚያ የሚሆን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት በመፍጠር እየሰራ ሲሆን፤ ጽ/ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በጽ/ቤቱ በብድር ፋይናንስ የተደረጉ የከተማ መጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ብዛት 62 የደረሱ ሲሆን፣ የብድር መጠኑም ከ6 ቢሊዮን ብር በላይ ደርሷል፡፡

የጽሕፈት ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ

ራዕይ

5. በ2017 ዓ.ም ለከተሞች የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን ልማት ግንባር ቀደም የፋይናንስ ተቋም መሆን፡፡

ተልዕኮ

6. የከተሞች የመጠጥ ውሃና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሽፋን ለማሳደግ እና የመስኖ ልማት ለማስፋፋት እንዲቻል ከተለያዩ የፋይናንስ ምንጮች የሚገኘውን የገንዘብ ብድር መስፈርቱን ለሚያሟሉ የከተሞች የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች እና ለመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ብድር መስጠትና ብድሩን በወቅቱ ሰብስቦ ለሌሎች ተመሣሣይ የልማት ሥራዎች ማስፈጸሚያ የሚሆን የተዘዋዋሪ ፈንድ /Revolving Fund/ ክምችት መፍጠር ነው፡፡

የጽሕፈት ቤቱ ዓላማ፣ ሥልጣን እና ተግባር

ዓላማ

7. በውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማሩ ተቋማት ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ችለው ለሕብረተሰቡ አስተማማኝ እና ዘላቂነት ያለው የውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤ የመስኖ ልማትን በማስፋፋትና ዘለቄታዊነቱን በማረጋገጥ በምግብ ራስን ለመቻል ለሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ማስቻል እና ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ዓላማዎች እውን ለማድረግ ወጪን በማስመለስ መርሆ /principle of cost recovery/ ላይ የተመሠረተ የረዥም ጊዜ ብድር ማበደር ነው፡፡

የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣን እና ተግባር

8. ጽሕፈት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 268/1994 (በ581/2000 እንደተሻሻለ) መሰረት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

- የቦርዱ ውሣኔዎችና መመሪያዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
- የፈንዱን ሂሣብና ሪኮርድ ይይዛል፣
- የቦርዱን ሥራ አመራር ስብሰባዎች ሪኮርዶች ይይዛል፣
- በየዓመቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በመገምገምና ቦርዱ በሚያወጣው የብድር አሰጣጥ አወሳሰን መመዘኛ መሠረት ቅደም ተከተል በማውጣት ከፈንዱ በብድር ይሰጣል፣
- ለፈንዱ መግባት የሚገባውን የብድር ተመላሽ እና በማቋቋሚያ አዋጁ በአንቀጽ 5 ከተጠቀሱት ምንጮች ማለትም ከፈንዱ ዓላማ ጋር በተያያዘ ከውጭ መንግሥታት እና ከዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ የገንዘብ እርዳታና ብድር፣ ከፌደራል መንግሥት ከሚመደብለት በጀትና ከልዩ ልዩ ምንጮች የሚገኘውን ተሰብሳቢ ገንዘብ ሁሉ በወቅቱ ይሰበስባል፣ በፈንዱ ሂሣብ ገቢ መደረጉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
- ፈንዱን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሣቦችን ለቦርዱ ያቀርባል፣
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፡፡

የቦርዱ ሥልጣን እና ተግባር

9. ቦርዱ በአዋጅ ቁጥር 268/1994 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

- ፈንዱን በበላይነት ያስተዳድራል፣
- ስለፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፣
- ለፈንዱ መግባት ያለባቸው ገቢዎች በወቅቱ መሰብሰባቸውን እና በፈንዱ ሂሣብ መግባታቸውን ያረጋግጣል፣
- በማቋቋሚያ አዋጁ አንቀጽ 7 ማለትም በፈንዱ ተጠቃሚ የሚሆን ተቋም ሕጋዊ ሰውነት ያለው መሆን አለበት ተብሎ የተደነገጉ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የብድር አሰጣጥ አወሳሰን መመዘኛዎችን ያወጣል፣

- የፈንዱን የኦዲት ሪፖርቶች ይገመግማል፣ በኦዲት ሪፖርቶቹ መሠረት ተገቢ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ያረጋግጣል፣ በኦዲተር የተመረመረ የፈንዱ ዓመታዊ ሂሣብ እንዲጠናቀርና ይፋ እንዲሆን ያስደርጋል፣
- ፈንዱ ሊያድግ የሚችልበትን መንገድ ይፈልጋል፣
- ከፈንዱ ጋር በተያያዘ በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ መንግስትን ያማክራል፣ ለመንግሥት አቅርቦ ያስጸድቃል፣
- የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት ይመረምራል፣ ለመንግሥት አቅርቦ ያስፀድቃል፣
- የጽሕፈት ቤቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ ለመንግሥት በማቅረብ ያሾማል፡፡

የጽሕፈት ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

ድርጅታዊ መዋቅር

10. ጽሕፈት ቤቱ በቦርድ የሚመራ ሲሆን ተጠሪነቱ ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ሲሆን፤ በቦርዱ አቅራቢነት በመንግስት የሚሾም አንድ ዋና ዳይሬክተር እና በስምንት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች የተደራጀ ነው፡፡ የጽሕፈት ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር በአባሪ 1 ተያይዟል፡፡

የሰው ኃይል

11. ጽሕፈት ቤቱ በ1994 በጸደቀው መዋቅር መሠረት 71 የሥራ መደብ ያለው ሲሆን በመስከረም ወር 2009 ዓ.ም ያለው የሰው ኃይል ወንድ 35 ሴት 21 በድምሩ 56 ሰራተኞች ናቸው፡፡ በስራ ላይ ያሉት ሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲገለጽ ሁለተኛ ዲግሪ 13 (23%)፣ የመጀመርያ ድግሪ 14 (25%)፣ ዲፕሎማ 8 (14%)፣ 12 ክፍልና ከዚያ በታች የትምህርት ደረጃ 21(38%) በጠቅላላ 56 ናቸው፡፡

የጽሕፈት ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

12. ጽሕፈት ቤቱ የተጣለበትን የሥራ ድርሻ ለማከናወን እና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተደራሽነቱን በማጠናከር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለመደገፍ ይረዳው ዘንድ የሚያስፈልገውን በጀት ከፈንዱ ዓላማ ጋር በተያያዘ ከውጭ መንግሥታት፣ ከዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የሚገኝ የገንዘብ እርዳታና ብድር፣ ከፌደራል መንግስት በሚመደብለት በጀት እና ከልዩ ልዩምንጮች ያገኛል፡፡ በዚህም መሠረት ከ2005

እስከ 2009 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ድረስ ያለው ገቢና ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

በጀት ዓመት	መደበኛ በጀት				ካፒታል (የብድር ፈንድ)			
	የተፈቀደ	ሥራ ላይ የዋለ	ልዩነት (ሥራ ላይ የዋለው በማነስ)	በመቶኛ	የተፈቀደ	ሥራ ላይ የዋለ	ልዩነት (ሥራ ላይ የዋለው በማነስ)	በመቶኛ
2005	3,581,100.00	2,372,586.32	1,208,513.68	66%	899,070,000.00	545,530,090.00	353,539,910.00	61%
2006	4,853,990.00	9,905,372.40	(5,051,382.40)	204%	932,592,000.00	587,827,620.00	344,764,380.00	63%
2007	5,825,591.62	4,411,129.56	1,414,462.06	76%	350,000,000.00	506,258,240.00	(156,258,240.00)	145%
2008	9292000.00	6863332.76	2,428,667.24	74%	450,000,000.00	785,351,340.00	(335,351,340.00)	175%
2009 (1ኛ ሩብ አመት)	972,838.68	769,930.69	202,907.99	79%	105,525,950.00	79,776,900.00	25,749,040.00	76%

መግለጫ፡-

1. የመደበኛ በጀት፡- አጠቃቀም በተመለከተ በ2005፣ በ2007 እና በ2008 ዓ.ም አጠቃቀሙ በማነስ የታየበት ምክንያት ከደመወዝና ተያያዥ ወጪዎችን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም ባለመቻሉ ሲሆን፣ ይህም የሆነው ባሉት ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ከገበያው የሚፈለገውን የሰው ኃይል ለማግኘት ባለመቻሉ ነው፡፡ የ2009 በጀት ዓመት የ1ኛ ሩብ ዓመት የተመደበ በጀት ለኳርተሩ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ተጠይቆ የመጣ ገንዘብ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡ እንዲሁም በ2006 ደግሞ አጠቃቀሙ በመብለጥ የታየበት ምክንያት ለጽ/ቤቱ የሰርቪስ አገልግሎትና ለ5 ከተሞች አገልግሎት ከውጭ ሀገር በግዥ ለገቡት 6መኪኖች የቀረጥ ክፍያ እንደተጨማሪ በጀት ተደርጎ ወጪው ስለተመዘገበ ነው፡፡
2. የብድር ፈንድ፡- አጠቃቀምን በተመለከተ በ2005፣ በ2006 እና በ2009 በጀት ዓመት በማነስ የታየበት ምክንያት የፕሮጀክቶቹ አስፈጻሚዎች ፕሮጀክቱን በታቀደው መሠርት እንዲፈጽሙ ባለማድረጋቸውና ክፍያ ባለመጠየቃቸው ሲሆን በ2007 እና በ2008 በጀት አመት በመብለጥ የታየበት ምክንያት ደግሞ የፕሮጀክቶቹ ባለቤቶች የፕሮጀክቱን ሥራ አከናውነው የክፍያ ጥያቄ ስላቀረቡ ከፈንድ በጀት፣ ከመዋጮ በጀትና ከሪቮልቪንግ ፈንድ የተጠየቀው ክፍያ ስለተፈጸመ በብልጫ ታይቷል፡ እንዲሁም የ2009 ዓ.ም 1ኛ ሩብ ዓመት የተመደበ በሩብ ዓመት ወጪ ይሆናል ተብሎ የታቀደ ነው፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

13. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ጽ/ቤቱ ለንፁህ መጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽን እና ለመስኖ ልማት ከተለያዩ ፋይናንሰሮች የሚሰበሰበው ገንዘብ በአግባቡ ለሚፈለገው ዓላማ መዋሉን፣ የብድር አስተዳደሩ በፍትሃዊነት ለሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ክፍፍል የሚደረግበትን ሁኔታ በማመቻቸት ዓላማውን ማሳካቱን እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋጋጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ችግሮቹን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

14. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

« *የውሃ ልማት ፈንድ ማመንጨትና ብድር አስተዳደር ውጤታማና አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ፤"*

የሚል ነው፡፡

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Crieria)

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች

15. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ሥር ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተመረጡ ሲሆን፣ እነርሱም፡-

1. ጽ/ቤቱ ፈንድ ማመንጨት ተግባሩን ለማከናወን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣
2. ጽ/ቤቱ የብድር አስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑ መገምገም፣
3. ጽ/ቤቱ ከፈጻሚ ባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋና ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ፣

የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

16. ከላይ የተመረጡትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issue) ለመገምገም የሚያስችሉ 27 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የጽ/ቤቱ የመቋቋሚያ አዋጅ፣ የጽ/ቤቱ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት /BPR/፣ የብድር ውል ስምምነቶች፣ የጽ/ቤቱ ዕቅድና ክንውን ሪፖርቶች፣ የሂሣብ አያያዝ መመርያ፣ የውስጥ ኦዲት ማንዋል፣ የቦርድና የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ፣ የጽ/ቤቱ የዜጎች ቻርተርና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ሥራው ለሚመለከታቸው የጽ/ቤቱ ኃላፊዎች ተልከው አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ (የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 2 ተያይዘዋል)፡፡

ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

የኦዲቱ ወሰን

17. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2005 እስከ 2008 በጀት ዓመት ያሉትን አራት ዓመታት እና የ2009 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

የኦዲቱ ዘዴ

18. ኦዲቱ በዋነኝነት የተከናወነው በውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ሲሆን የኦዲት ቡድኑ ከተለያዩ ፋይናንሰሮች የሚሰበሰበውን ገንዘብ ከመሰብሰብ፣ ብድር ከማበደርና ከማስመለስ ጋር ተያያዥ የሆኑ የጽ/ቤቱን አሰራር የሚመለከቱ የተለያዩ አዋጆች፣ የሂሳብ ሰነዶችና ማስረጃዎችን፣ የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት፣ የየዓመቱን ዕቅድና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፣ የስትራቴጅክ ዕቅድ (ከ2003-2007 እና 2008-2012)፣ የቦርድ ቃለ-ጉባኤ፣ የሥራ አመራር (የማናጅመንት) ስብሰባ ቃለ- ጉባኤ፣ የብድር ውል ስምምነቶች፣ የጽ/ቤቱ የዜጎች ቻርተር፣ ጽ/ቤቱን የሚመለከቱ የወጡ ብሮሸሮች፣ በጽ/ቤቱና በተለያዩ አካላት የተጠኑ የጥናት ሰነዶችና መመሪያዎች

ተከልሰዋል፣ የሚመለከታቸውን የጽ/ቤቱን የሥራ ኃላፊዎች ቃለ- መጠይቅ በማቅረብና ማስረጃዎችን የመከለስ ሥራዎች ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም የጽ/ቤቱ ባለድርሻ አካላት ከሆኑት የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

19. በተጨማሪም በኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮዎችና ስምንት የከተሞች ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማት በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ማስረጃዎችን ጠይቆ በመከለስ እና በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበው ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ባለድርሻ አካላት እና የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማት ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

የሥራ ፍሰት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION)



ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

2.1 የጽ/ቤቱ ፈንድ ማመንጨት ሂደት ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፤

ጽ/ቤቱ ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት የፕሮጀክት ፕሮፖዛል /ፕሮፋይል/ ስለማዘጋጀቱ፣

20. ጽ/ቤቱ ወጭን በማስመለስ መርሆ ላይ የተመሰረተ የረዥም ጊዜ ብድር ለመስጠት እንዲቻል ባዘጋጀው የዜጎች ቻርተር መሰረት ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት ፕሮጀክት የሚሆን የፕሮጀክት ፕሮፋይል አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብና ክትትል በማድረግ ፋይናንስ ሊያፈላልግ ይገባል፡፡

21. ጽ/ቤቱ ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት የፕሮጀክት ፕሮፋይል አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያላቀረበና ለዚህ አገልግሎት የሚሆን ፋይናንስ የማፈላለግ ሥራ ያልሰራ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው የሳኒቴሽን አገልግሎት የወጪ አመላለስ አጠቃላይ የህግ ማዕቀፍ የሌለው መሆኑ፣ ጽ/ቤቱ ከተሰጠው ኃላፊነት አንጻር በመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተካተው የሚቀርቡትን እንደ ሕዝብ ሽንት ቤት፣ የህዝብ ሻወር ቤት፣ እና የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ (ድራይ ቤድ) ዓይነት የሚሰራ መሆኑን እና ለብቻው የፕሮጀክት ፕሮፖዛል (ፕሮፋይል) ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ እንዳልተገኘ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የመስኖ ልማት ፕሮጀክትን በተመለከተ በሴክተር ደረጃ ግልጽ የሆነ የወጪ አመላለስ ደንብም ሆነ መመሪያ ስላልተቀመጠለት የፕሮጀክት ፕሮፖዛል (ፕሮፋይል) በጽ/ቤቱ እንዳልተዘጋጀ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ይስጡ እንጂ ለዜጎች እንተገብረዋለን ብለው ቃል የገቡ ከመሆኑም በተጨማሪም ደንብም ሆነ መመሪያውን በማዘጋጀት እና በሚመለከተው አካል በማጸደቅ ወደሥራ መግባት ይቻል ስለነበረ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

23. ጽህፈት ቤቱ ከተቋቋመበት ዓላማ እና በዜጎች ቻርተር በተገለጸው መሰረት ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት ፕሮጀክት የፕሮጀክት ፕሮፋይል በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል በማቅረብ ፋይናንስ የማይፈለግ ከሆነ ለሕብረተሰቡ

አስተማማኝ እና ዘላቂነት ያለው ሳኒቴሽን አገልግሎት እንዳያገኙ ሊያደርግ የሚችል እና አነስተኛና መካከለኛ የመስኖ ልማትን በማስፋፋትና ዘለቄታዊነቱን በማረጋገጥ በምግብ ራስን ለመቻል ለሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ አስተዋጽኦ ሊያሳድር ይችላል፡፡

የጽ/ቤቱን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን ያስጠና መሆኑ በተመለከተ፣

24. የጽ/ቤቱን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በማጥናት/በማስጠናት ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በማጸደቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡

25. ጽ/ቤቱ የተዘዋዋሪ ፈንድ (Revoleving Fund) ክምችትን ለማጠናከር የሚረዱ ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን ያላጠና ወይም ያላስጠና መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

26. ስለሁኔታው የጽ/ቤቱ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ጥናቱን ለማዘጋጀት ቀደም ብለው ያቀዱ ቢሆንም ጽ/ቤቱ ባለበት ከፍተኛ የባለሙያ ዕጥረት ምክንያት ያሉት ጥቂት ባለሙያዎች በሌሎች ቅድሚያ በሚሰጣቸው አጣዳፊ ሥራዎች ስለተጠመዱ ጥናቱ ተግባራዊ ሊሆን አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

27. ጽህፈት ቤቱ የፈንዱን የገቢ ምንጮች በተለያየ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎች በማጥናት ወይም በማስጠናት በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ አለማድረጉ የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችቱ እንዳያድግ በማድረግ ከፈንዱ ድጋፍ የሚፈልጉ በወቅቱ ገንዘቡን እንዳያገኙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰበው ገንዘብ ምዝገባን በተመለከተ፤

28. ጽ/ቤቱ ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰበውን ገንዘብ የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በጠበቀ ሁኔታ መሰረት በወቅቱ ተከታትሎ ሊመዘግብ ይገባል፡፡

29. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ካየናቸው የሂሳብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች ለመረዳት እንደቻልነው፡-

- ከ6 ከተሞች (ሆሳዕና፣ ቡታጅራ፣ ወልቂጤ፣ ሰበታ፣ አሶሳ እና ቡራዩ ከተማ) መሰብሰብ ያለበት የፕሮጀክት መዋጮ መካከል የአመዘጋገብ ልዩነት (ሁለት የተለያየ መግለጫ መቅረቡ) መኖሩ፡- (ዝርዝሩ በአባሪ 4 ላይ ተያይዟል)፡፡

- የሚዛን አማን ከተማ ውሃ አገልግሎት ለሚያከናውነው ፕሮጀክት ማዋጣት ያለበትን መዋጮ በቦርዱ ስብሰባ ላይ በ14/08/2001 ዓ.ም በተያዘው ቃለ ጉባኤ ቁጥር 47 ላይ የፕሮጀክት መዋጮ ብር 16,122,421.04 (አስራ ስድስት ሚልየን አንድ መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አራት መቶ ሃያ አንድ ብር ከአራት ሳንቲም) እንደተከፈለ የተገለጸ ቢሆንም በሌጀር ላይ ተመዝግቦ ያልተገኘ መሆኑ፣
- የክብረ-መንግስት፣ ሚዛን አማንና የሐረር ፕሮጀክት የብድር ስርጭትንና የፕሮጀክት መዋጮን በተመለከተ የተመዘገበበት ሌጀር ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በመንግስት ድጎማ በጀት ፋይናንስ የተደረገው የአክሱም ከተማ፣ በጣልያን መንግስት ፋይናንስ የሚደረጉ የ5 ከተሞች እና በዓለም ባንክ ብድር ፋይናንስ የሚደረጉ 20 ከተሞች ለብድር ተመላሽ የሚያገለግል ለእያንዳንዳቸው ሌጀር እንደተዘጋጀላቸው ቢገለጽም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤
- ጽ/ቤቱ የፈንዱ ሂሳብ በመንግስት ሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ሂሣቡን መዝግቦ በመያዝ ወርሃዊ፣ የሩብ አመትና አመታዊ ሪፖርት እየሰራ ለሚመለከተው አካል ስለማቅረቡ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ መረጃው ያልቀረበ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

30. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው የምዝገባ ግብዓቶችን ከሌጀሩ ጋር በማስተያየት ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑና ከዚህም ጋር ተያይዞ ከመነሻ ሰነዱ ጋር በቁጥር (በመጠን) የተለየ ምዝገባ ካለ ለማስተካከል ዝግጁ መሆናቸውን፣ እንዲሁም በፋይናንስ ክፍል በኩል የፕሮጀክቶች ገቢና ወጪ ሂሳብ የሚመዘገበውና የሚያዘው በተለያዩ ባለሙያዎችና ኮምፒውተሮች ላይ ስለሆነ በአንድ ማዕከል ያልተጠቃለለ በመሆኑ ችግሮች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ፣ የሀረር፣ ሚዛን፣ ክብረመንግስት ከተሞች ለጽ/ቤቱ የመጀመርያ ፕሮጀክቶች ስለሆኑ በወቅቱ ከመደበኛ ፋይናንስ ጋር በአንድ የባንክ አካውንት ሲከፍል የቆየ ስለሆነ ከፊሉ ደግሞ ለፕሮጀክት ተፈቅዶ በተከፈተው የፈንድ ባንክ ሂሣብ ሲከፍል የነበረ ስለሆነ በወቅቱ ማቅረብ እንዳልቻሉ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

31. ይሁን እንጂ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ይቀርባሉ የተባሉት ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ረቂቅ ሪፖርቱ እስኪጠናቀቅ ማስረጃዎቹ ያልቀረቡ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

32. ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስበውን ገንዘብ ትክክለኛ እና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብትን ከደጋፊ ሰነዶች ጋር በመያዝ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ በወቅቱ በትክክል የማይመዘገብ ከሆነ ሂሣቡን በወቅቱ ዘግቶ ኦዲት ለማስደረግ የማያስችልና በትክክል የፈንዱ ሂሳብ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ እንዳይቻል ከማድረጉም በላይ የጽ/ቤቱን የሂሣብ አያያዝ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

የፈንዱን ሂሣብ በውጭ ኦዲተሮቸ ኦዲት መደረጉን በተመለከተ፣

33. ጽ/ቤቱ የፈንዱን ሂሳብ የሂሳብ መግለጫዎች በማዘጋጀት በየአመቱ ኦዲት በማስደረግ የኦዲት ሪፖርቶቹ ለቦርዱ እንዲቀርቡ ማድረግ አለበት፡፡ በቀረቡት የኦዲት ሪፖርቶች ላይ በሚሰጡ አስተያየቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረትም ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ መደረግ አለበት፡፡

34. ጽ/ቤቱ የፈንዱን ሂሣብ በየአመቱ በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት ማስደረግ ያለበት ቢሆንም የፈንዱ ሂሣብ ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

35. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት የፈንዱን ሂሣብ ለማስመርመር ቀደም ሲል እንቅስቃሴ ጀምረው የነበረ ቢሆንም የተለያዩ ፕሮጀክቶች ሂሣብ በተለያዩ ባለሙያዎችና ኮምፒውተሮች የሚያዙ ስለሆነ የተጀመረው ሶፍት ዌር ሥራ ሲጠናቀቅ የፈንድ ሂሣቡ ወደ አንድ ቋት በጽ/ቤቱ ስም ተጠቃሎ እንዲያዝ በማድረግ ለኦዲት ሥራው የሚፈለጉትን ስቴትመንቶች አዘጋጅቶ ኦዲቱን ለማከናወን ታስቦ የነበረ ቢሆንም የሶፍት ዌሩ ሥራ በአንዳንድ ችግሮች የተነሳ ባለመጠናቀቁ የኦዲት ሥራው እንደታሰበው ሊከናወን አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

36. የፈንዱ ሂሳብ በየአመቱ እየተዘጋ እና የሂሳብ መግለጫዎች እየተዘጋጁ በየአመቱ ኦዲት ባለመደረጉ ጽህፈት ቤቱ ከፋይናንስ አሰራር ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ የአሰራር ስህተቶችን ወይም ድክመቶችን እንዳያርም፣ በኦዲት ሪፖርቱ በሚቀርቡ ግኝቶች ላይ በወቅቱ እርምጃ እንዳይወስድና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር

እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ አበዳሪና ለጋሽ ተቋማት በጽህፈት ቤቱ በሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት ላይ ጥርጣሬ እንዲፈጠር ሊያደርግ ይችላል፡፡

2.2 ጽ/ቤቱ የብድር አስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ ስለመሆኑ፣

ጽ/ቤቱ የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመርያ አዘጋጅቶ በቦርድ በማጸደቅ ብድር የሰጠ መሆኑን በተመለከተ፤

37. ጽ/ቤቱ በአዋጅ 268/1994 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛ መመሪያ በማዘጋጀት በቦርድ እንዲጸድቅ ማድረግ አለበት፡፡ እንዲሁም በቦርዱ በጸደቀው የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛ መሰረት ጽ/ቤቱ ለውሃ አቅርቦት፣ ሳኒቴሽን እና ለመስኖ ልማት ሥራ አገልግሎት የሚሆን በየመቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በመገምገም ለተበዳሪዎች ብድር መስጠት አለበት፡፡

38. ጽ/ቤቱ ብድር ለመስጠት የሚያገለግል ረቂቅ መመሪያ በሚያዝያ ወር 2001 ዓ.ም የተዘጋጀ ሲሆን ረቂቅ መመሪያው በ14/08/2001 ለቦርድ ስብሰባ ቀርቦ በቀድሞው ውሃ ሀብት ሚኒስቴር በህግ ባለሞያ እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ከተገመገመ በኃላ ለቦርዱ እንዲቀርብ በተደጋጋሚ ቢወሰንም (የቦርድ ቃለ ጉባኤ 47 እና 76) በውሳኔው መሰረት ተስተካክሎ እንዲጽድቅ ያልተደረገ፣ ነገር ግን ባልጸደቀው ረቂቅ መመሪያ ለተበዳሪ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማት ጽ/ቤቱ ብድር እየሰጠ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

39. ስለጉዳዩ የጽ/ቤቱ ኃላፊ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፡-

- በጽ/ቤቱ በኩል በወቅቱ የተሰጠውን መመሪያ አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ በማድረግ በኩል መዘግየት እንደነበረ የሚታወቅ ቢሆንም ረቂቁ ከተዘጋጀ በኋላ ግን ቦርዱ በየጊዜው በሚሰጠው አዳዲስ የማሻሻያ ሀሳቦችና አስተያየቶች ምክንያት እስካሁን ተጠናቆ ሊጸድቅ አለመቻሉን፤
- ቦርዱ በየመቱ በሚያጸድቀው የበጀት ዓመቱ ዕቅድ መሠረት ለተበዳሪ ከተሞች ብድር እየሰጠ እንደሚገኝ እና የተለየ መመሪያ ሊዘጋጅለት ይገባል ከተባለ ለወደፊቱ መመሪያው እንዲጠና ተደርጎ ሥራ ላይ እንዲውል እንደሚደረግ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

40. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ በጽ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ 268/1994 አንቀጽ 14/2 (የተሻሻለው አዋጅ 581/2000 አንቀፅ 6) ቦርዱ ስለፈንዱ አሰባሰብና ከፈንዱ

ገንዘብ ወጪና ተከፋይ ስለሚሆንበት ስርዓት መመሪያ እንደሚወጣና በጸደቀው መመሪያ መሰረት ብድር መሰጠት ያለበት በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

41. ጽህፈት ቤቱ የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመሪያ በማውጣት ሥራ ላይ ባለማዋሉ በጽ/ቤቱ የሚሰጠውን ብድር የተቀላጠፈና ግልጸኝነት የጎደለው እንዲሆን እንዲሁም ብቁና አስተማማኝ የብድር አስተዳደር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ቦርዱ ባጸደቀው የብድር አሰጣጥ መመዘኛ መሠረት በያመቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በመገምገም ብድር የማይሰጥ ከሆነ የተበዳሪዎችን የብድር ፍላጎት ለማሟላትና የሚቀርበውን ብድር ጥያቄዎች ግልጽነት በተሞላበት ሁኔታ በመገምገምና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዳይስተናገዱ ያደርጋል፡፡

በጽ/ቤቱ የብድር ተጠቃሚ ከተሞችን ለመምረጥ የሚያስችል የከተሞች መምረጫ መስፈርት ስለመኖሩ፣

42. በጽ/ቤቱ የብድር ተጠቃሚ ለሚሆኑ ከተሞችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ የከተሞች መምረጫ መስፈርት መመርያ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

43. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በጽህፈት ቤቱ የብድር ተጠቃሚ ለሚሆኑ የከተሞች መምረጫ መስፈርት መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡ የብድር ተጠቃሚ ከተሞች መምረጫ መመሪያ ባለመውጣቱ ፍትሃዊነት በጎደለው መልኩ አቅም ላላቸው ከተሞች ነጻ ግንባታ የሚካሄድበትና ለትናንሽ ከተሞች በብድር ፈንድ እንዲታቀፉ የሚሰራበት የተዘበራረቀ አሰራር የፈጠረ መሆኑን ሚያዚያ 27/2007 ዓ.ም በተካሄደው 76ኛ የቦርድ ስብሰባ ከተያዘው ቃለ ጉባኤ ለመረዳት ተችሏል፡፡

44. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ጽ/ቤቱ እየተጠቀመበት ያለው የከተሞች (Borrower's Eligibility Criteria) እና የፕሮጀክት አዋጭነት መገምገሚያ መስፈርቶች (Project's Appraisal Criteria) መሰረት አሟልተው ለሚቀርቡ ከተሞች ብድር ሚሰጥ መሆኑን ጠቅሰው የትኞቹ ከተሞች በብድር ወይም በነጻ /በድጎማ ተጠቃሚ መሆን አለባቸው የሚለውን ሀገር አቀፍ መመዘኛና መመሪያ የማዘጋጀት ኃላፊነት ያለበት የሴክተሩ ፖሊሲ አስፈጻሚ የሆነው የውሃ መስኖና ኤሌትሪክ ሚኒስቴር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

45. ጽ/ቤቱ የከተሞች መምረጫ መስፈረት መመሪያ እንደሚያዘጋጅ በጽ/ቤቱ መዋቅር የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ስራ ሂደት ክፍል ተ/ቁ 5 ላይ እንደ አንድ የሥራ ድርሻ የተገለጸ በመሆኑና በሌላ በኩል መመሪያው ባለመውጣቱ የተዘበራረቀ የአሰራር ችግር የፈጠረ እና የቦርዱም ስጋት በመሆኑ መመሪያውን በማዘጋጀትና

የሚኒስቴር መ/ቤቱን ሀሳብ በማካተት እንዲጸቅ ለቦርዱ ማቅረብ ይቻል የነበረ በመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት አልተቀበልነውም፡፡

46. በጽህፈት ቤቱ የብድር ተጠቃሚ ከተሞች መምረጫ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጅቶ እንዲጸድቅና ሥራ ላይ እንዲውል ባለመደረጉ ግልጽና ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር ከማድረጉም በላይ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ባሉ ብድር ተጠቃሚ ከተሞች ላይ ቅሬታ ሊፈጥር ይችላል፡፡

ከተበዳሪ ተቋማት የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ (Matching Fund) በወቅቱ መሰብሰቡን በተመለከተ፡፡

47. በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ተበዳሪ ተቋማት ከእነርሱ የሚጠበቀው የፕሮጀክት መዋጮ (Matching Fund) ለጽ/ቤቱ ሊከፍሉ ይገባል፤ ጽ/ቤቱም ከተበዳሪዎች ለሚሰበስበው የፕሮጀክት መዋጮ (Matching Fund) የብድሩን መጠን ስንት መቶኛ(ፐርሰንት) ማዋጣት እንደሚገባቸው የሚወስን ግልጽ መስፈርት ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም በወቅቱ ያልተከፈለ መዋጮ ካለ እየተከታተተለ በወቅቱ ሊሰበስብ ይገባል፡፡

48. ይሁን እንጂ ጽ/ቤቱ ከተበዳሪዎች ለሚሰበስበው የፕሮጀክት መዋጮ (Matching Fund) የብድሩን መጠን ስንት መቶኛ(ፐርሰንት) ማዋጣት እንደሚገባቸው የሚወስን ግልጽ መስፈርት አዘጋጅቶ ተግባራዊ አላደረገም፡፡ በተጨማሪም በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ከተበዳሪ ተቋማት የፕሮጀክት መዋጮ በወቅቱ እየተከታተለ የማይሰበስብ መሆኑ ታውቋል፡፡ በኦዲት ወቅት በናሙና ከታዩ ተበዳሪ ተቋማት ውስጥ ፡-

- በዓለም ባንክ ፋይናንስ የተደረጉ ስድስት ከተሞችን በተመለከተ ወልቂጤ በ2003፣ ቡታጅራና ሆሳዕና በ2006፣ እንዲሁም አሶሳ በ2007 ዓ.ም የተጠናቁ ቢሆንም ከወልቂጤ ብር 3,716,216.73 ከሆሳዕና ብር 6,923,158.15 ከቡታጅራ ብር 2,715,529.00 ከአሶሳ ብር 1,644,866.60 በጠቅላላው ብር 14,999,770.48 እስካሁን ድረስ ያልተሰበሰበ የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ መኖሩ፤ (ዝርዝሩ በአባሪ 5 ተያይዟል)፡፡
- ለሐረር፣ ክብረመንግስትና አክሱም ፕሮጀክት ምንም የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ ያላዋጡ መሆናቸው፣
- የሰበታ ከተማ ብር 5,121,713.50 እና የቡራዩ ከተማ ብር 1,861,704.00 በብልጫ እንዲከፍሉ መደረጉ፤

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

49. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፣ የፕሮጀክት መዋጮ በወቅቱ ተጠቃሎ መግባት እንዳለበት እንደሚያምኑና የስድስቱ ከተሞች ከዓለም ባንክ በዶላር የተመደበው ገንዘብ በጊዜው የነበረው ምንዛሪ ለውጥ የተነሳ የብር መጠኑ (Foreign Exchange) በመጨመሩ ምክንያት የተመደበላቸው የብድር ገንዘብ ከፍተኛውን የፕሮጀክት ወጪያቸውን መሸፈን በመቻሉ ቀደም ብሎ እንደታሰበው የመዋጮ ገንዘቡን ሙሉ በሙሉ ማዋጣት እንደማያስፈልጋቸው በመታመኑ እንደሆነ፣ በብልጫ ያዋጡት እንደ ቡታጅራ የመሳሰሉት ለብድር ክፍያ እንዲውልላቸው ሲደረግ ሌሎቹ ደግሞ በእንጥልጥል ላይ ያሉ የፕሮጀክቶቻቸው ወጪዎች ሙሉ በሙሉ ተጣርተው ሂሳባቸው ሲዘጋ ቀሪ መዋጮ ሂሳብ ካላቸው ለብድር መክፈያ እንዲውል ለማድረግ አለበለዚያም ደግሞ የሚፈለግባቸው መዋጮ ካለ እንዲያስገቡ ለማድረግ ማሰባቸውን፣

- የአክሱምን ፕሮጀክት በባለቤትነት ያሰራው የክልሉ መንግስት ሲሆን ከፍተኛውን ወጪ በቀጥታ ራሱ በጀት አስይዞ ያሰራው መሆኑን፣
- የክብረመንግስት ፕሮጀክትም ከውጭ ፋይናንሰሩና ከፌደራሉ መንግስት የተመደበው በጀት በቂ ይሆናል ተብሎ ስለታመነበት መዋጮ ያልተጠየቁ መሆኑን፣
- የሐረር ከተማ ፕሮጀክት መጀመርያውኑ ከብር 60 ሚልየን በላይ የሚያወጣ ቧንቧ ገዝቶ ለፕሮጀክቱ ያዋለ ሲሆን ወደ የፕሮጀክቱ መጨረሻ ላይ ደግሞ ብር 3 ሚሊየን የሚሆን ገንዘብ በመዋጮነት ለፕሮጀክቱ መዋሉን፣ ገልጸዋል፡፡

50. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ የሐረር ከተማ 3 ሚልየን ብር የፕሮጀክት መዋጮ እንዳዋጣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የገለጹ ቢሆንም ማስረጃው እንዲቀርብ ተጠይቆ ባለመቅረቡ እንዲሁም የትኛውም ተበዳሪ ተቋም ለመበደር የብድሩን መጠን ስንት መቶኛ(ፐርሰንት) ማዋጣት እንደሚገባቸው የሚገልጽ መስፈርት ባለመኖሩ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

51. ከጽህፈት ቤቱ ብድር የሚወስዱ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማት የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ የማያዋጡ፣ የተዋጣውም ገንዘብ በወቅቱ የማይሰበስብ ከሆነ ጽህፈት ቤቱ የተዘዋዋሪ ፈንዱን አቅም እንዳያድግ በማድረግ ብድር ለመስጠት ያለውን የካፒታል አቅም የሚቀንስ፣ ፕሮጀክቱ በወቅቱ ተገንብቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል

የማያስችለው ከመሆኑም በላይ በብድር የሚገነባውን ፕሮጀክት ህብረተሰቡ የባለቤትነት ስሜት እንዳይኖረው አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ከተበዳሪዎች መሰብሰብ የሚገባውን የብድር ተመላሽና ወለድ በወጣው መርህ ግብር መሠረት የተሰበሰበ መሆኑንና በወቅቱ ያልተሰበሰበ ብድር ሲኖር እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፤

52. በአዋጁ 581/2000 አንቀፅ 6 መሰረት ጽ/ቤቱ ከተበዳሪዎች መሰብሰብ የሚገባውን የብድር ተመላሽና ወለድ በወቅቱ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ የወሰዱትን ብድር በወቅቱ በማይከፈሉ ተበዳሪ ተቋማትም ላይ በውሉ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

53. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ከጽ/ቤቱ ቅድሚያ አግኝተው ከተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ውስጥ ያልተሰበሰበ የብድር ተመላሽና ወለድ በድምሩ ብር 111,954,101.70 (አንድ መቶ አስራ አንድ ሚልዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሣ አራት ሺህ አንድ መቶ አንድ ብር ከሰባ ሳንቲም) መኖሩን ከቀረቡት ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ (ዝርዝር መረጃው በአባሪ 6 ተያይዟል)፡፡
- ለቆጋ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ 37.84 ሚልዮን ዩሮ ወጪ የወጣ ቢሆንም ወጪውን ለማስመለስ የሚያስችል ጥናት እንዲጠና በመወሰኑ በሁለት አማካሪ ተቋማት ተቀጥረው ጥናቱ እንደተካሄደ በቀን 27/08/2007 ዓ.ም በተካሄደ የቦርድ ቃለ-ጉባኤ ቁጥር 76 ላይ የተገለጸ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ያልተሰበሰበ መሆኑን፣
- የቆጋ መስኖ ልማትና ተፋሰስ እንክብካቤ በቀን 10/12/2003 ዓ.ም ባካሄደው 19 መደበኛ ስብሰባ ላይ የቆጋ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የፕሮጀክቱ ዋጋ ምለሳ ጥናት የገበያ ሁኔታውን በተወሰነ ደረጃ የዳሰሰ ቢሆንም ወደ ዋጋ ምለሳ ሊያስገባ የማያስችል መሆኑ ቀደም ሲል በታመነበት መሰረት የገበያ ጥናቱ በተሟላ ሁኔታ በ2004 በጀት ዓመት ተጠናቆ በውጤቱ ላይ በመመስረት በ2005 ዓ.ም ዋጋ ምለሳ እንዲጀምር የፕሮጀክት የበላይ ሥራ አመራር አብይ ኮሚቴ የተወሰነ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ጽ/ቤቱ የዋጋ ማስመለስ ሥራ ያልሰራ መሆኑ፤
- የጽህፈት ቤቱ ብድር የመሰብሰብ አቅም ከአመት አመት እየቀነሰ የመጣ መሆኑን፣ ለዚህም እንደ ማሳያ እንዲሆን ከ 2006 እስከ 2009 የመጀመሪያ ሩብ በጀት አመት ያለው የብድር አመላለስ የሚያሳይ ግራፍ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡



ብድር የመሰብሰብ አቅም ከአመት አመት እየቀነሰ የመጣ መሆኑንየሚያሳይ ግራፍ

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

54. ከዚህ በተጨማሪ ጽ/ቤቱ ከከተሞች ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ጋር በገባው የብድር ውል ስምምነት መሰረት በወቅቱ ብድር በማይከፍሉ ተበዳሪ ከተሞች ላይ በብድር ውሉ መሰረት መቀጣት እንዳለባቸው በውሉ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም ጽ/ቤቱ የማያስከፍል መሆኑ ታውቋል፡፡

55. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፡-

- በወቅቱ ያልተሰበሰቡ የብድር ተመላሽ ሂሳቦችን በተመለከተ ተበዳሪ ከተሞች በተዘጋጀላቸው ጊዜ ሰሌዳ መሰረት ገቢ እንዲያደርጉ በቅድሚያ በስልክና በደብዳቤ በማሳወቅ ክትትል እንደሚያደርጉ ሆኖም ግን አንዳንድ ከተሞች በተደጋጋሚ እንዲከፍሉ ቢጠየቁም ከሁለት እስከ ሶስት ያህል ክፍያዎች ያዘገዩ ተበዳሪ ከተሞች መኖራቸውን፣ በተጨማሪም ጽ/ቤቱ በውሉ መሰረት ወደ ቅጣትና ክስ ከመሄዱ በፊት የግምገማና ክትትል ቡድን አቋቁሞ ክትትል የጀመረ መሆኑን፣
- ለቆጋ መስኖ ፕሮጀክት ቀጥተኛ ባለቤትና አስፈጻሚ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ስለሆነ የብድር ተመላሹን ማስመለስ አለመቻላቸውን፣
- በተገባው ውል መሰረት ብድራቸውን በወቅቱ ባልከፈሉት ላይ ተጨማሪ የወለድ ቅጣት እንዲከፍሉ አልተደረገም፡፡ ምክንያቱም ብድራቸውን በመክፈል በኩል ያጋጠማቸውን ችግር ተገቢውን ዳሰሳ ስላላደረግን ቅጣቱን መጫን አግባብ እንዳልሆነና የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ስለሆኑ ተጨማሪ ቅጣት ከጫንባቸው ዞሮ

ዞሮ የታሪፉ ጫና የሚያርፈው በተጠቃሚው ህብረተሰብ ላይ ስለሆነ እስካሁን ድረስ እንዳልተቀጡ፣

ገልጸዋል፡፡

ኃላፊው ይህን ይበሉ እንጂ በወቅቱ በማይከፍሉት ላይ በውሉ መሰረት እርምጃ በመውሰድ ገንዘቡን ማስከፈል ስለነበረባቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

56. የብድር ተመላሽና ወለድ በሰዓቱና በወቅቱ የማይሰበሰብ ከሆና ብድር ለመውሰድ የሚጠባበቁ ከተሞችን በሰዓቱ ብድር እንዳይወስዱ ከማስቻሉም በላይ የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችቱ (Revoleving Fund) እንዳይዳብር ሊያደርግ ይችላል ፡፡ ጽህፈት ቤቱ በያመቱ ለፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚሰጣቸውን ብድር በብድር መርሀ-ግብር መሰረት እርምጃ ካልወሰደና የህግ ማዕቀፉ አስገዳጅነት ከሌለው የብድር አመላለሱ እንዲዘገይና እንዳይመለስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ብድር ለመጠየቅ ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የአዋጭነት ጥናቶችና ዲዛይኖች ተግባራዊ መሆናቸውን በተመለከተ፤

57. ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎች በቅድሚያ የአዋጭነት ጥናት ሰነዶቹ ወቅታዊና ተግባራዊ መሆናቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በተጠናው ጥናት መሰረት ለፕሮጀክቱ ሊተገበር የሚችልና ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ ዲዛይን ተሰርቶለት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

58. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- በሁሩታ ከተማ ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ የተጠናቀቀ ቢሆንም በቂ ዲዛይን ያልተሰራለት በመሆኑ ለተጨማሪ ወጪና መንጓተት በመዳረጉ እስካሁን ድረስ አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣ ለዚህ አይነተኛ ምክንያቱ ደግሞ መስመሩ ትክክለኛ የውሃ ስርጭት እየሰጠ ባለመሆኑ ህዝቡ የውሃውን ታሪፍ በመቃወም ቢል አለመግዛቱን የሁሩታ ከተማ የመጠጥ ውሃ ፍሳሽ አገልግሎት ተቋም ለውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት በደ/ቁጥር H/B/D/485/2008 በቀን 11/2/2008 የገለጹ መሆኑን፤
- የወልቂጤ ከተማ የፓይፕ ፍንዳታና መስመር ዋና ችግር ሲሆኑ በቀጣይ ትኩረት የሚሰጠው የቦዝባር ምንጭ የውሃ ተቋም የዲዛይን እና የፓምፕ ለውጥ ካልተደረገ በተደጋጋሚ የፓምፕ መቃጠልና መበላሸቱ ሊቀጥል እንደሚችል የዘርፉ ባለሙያዎች መግለጻቸውን እና ከብድር አመላለስ ጋር ተያይዞ ችግር እንደፈጠረባቸው ለውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት

በደ/ቂ/ወውአ/655/2008 በቀን28/08/2008 ዓ.ም በጻፉት ደብዳቤ የገለጹ መሆኑን፤

በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

59. እንዲሁም በናሙና ተመርጠው የታዩ የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋም የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽና የቀረቡት ማስረጃዎች በሚከለሱበት ወቅት ለጽ/ቤቱ የቀረቡና አዋጭ ናቸው ተብለው ጥናትና ዲዛይን ከተሰራላቸው ውስጥ፡-

- የሰበታ ከተማ ፕሮጀክት ትክክለኛ ጥናት ባለመደረጉ 2500 m3 ስፋት ያለው የውሃ ማጠራቀሚያ መገንባት ባልነበረበት እና ተጠቃሚ በሌለበት በዳማ ቀበሌ 05 መገንባቱ፣
- ቡራዩ ከተማ በቂ የሆነ ጥናት ያልተሰራለት በመሆኑ ለተጨማሪ ወጪና መንጓተት መዳረጉን፣ በቡራዩ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋም ከተሰሩት ስምንት የውሃ ጉድጓዶች ውስጥ አንዱ ጉድጓድ የደረቀ ሲሆን በቀበሌ 18 እና መስኪድ አካባቢ የሚገኙ ሁለት ጉድጓዶች 12.5L/S ይሰጥ የነበረው ወደ 5L/S መውረዱ፣ አንድ ጉድጓድ 19L/S ይሰጥ የነበረው ወደ 8L/S መውረዱ፣ አንድ ጉድጓድ 8L/S ይሰጥ የነበረው ወደ 4 L/S መውረዱ በቀረበላቸው መጠይቅ ላይ የገለጹ መሆኑ፤
- በዱራሜ ከተማ ፕሮጀክቱ ሰኔ 22 ቀን 2006 ዓ.ም የተጠናቀቀ ቢሆንም ከአንድ አመት በላይ አገልግሎት ያልሰጠ ሲሆን ስለሁኔታው የዱራሜ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋም ተጠይቆ በሰጠው መልስ በቂ ጥናት ያልተደረገለት በመሆኑ፣ ሁለት ጉድጓዶች ከፍተኛ የአይረን መጠን ያላቸው በመሆኑ ለተጨማሪ ወጪና መንጓተት መዳረጋቸውን እና ሙሉ በሙሉ አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑን በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ወቅት መግለጻቸው፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

60. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ተጠይቀው በሰጡት አስተያየት፡-

- የሰበታና የቡራዩ ከተሞች የፕሮጀክት ጥናትና አዋጭነቱ የተገመገመው ዕውቅና ባለው አማካሪ ድርጅት ነው፡፡ የሁለቱም የፕሮጀክት ባለቤት የክልሉ ቢሮ ስለሆነ ጽ/ቤቱ በግንባታ ወቅት ለሚከሰተው ጉድለቶች ሊጠየቅ እንደማይገባ

እንዲሁም የቡራዩ የውሃ መድረቅና የውሃው መጠን መቀነስ የከርሰምድር የውሃ ምንጭን (Unforeseen risk ground water utilization) ከመጠቀም አንጻር ሊያስወግዱት እንደማይችሉ፣

- በዱራሜ ከተማ ፕሮጀክቱ አልፎ አልፎ የመብራት መቆራረጥ እንዳለበት አውቀው ችግሩን በጋራ እየፈቱ እንደሆነ፣
- በሁሩታ ከተማ ፕሮጀክቱ ችግር በአሁን ሰዓት እንደተፈታና ለህብረተሰቡ የታሪፍ ማሻሻያ ስላልተገለጸ ይህን የታሪፍ ማሻሻያ ለመስራት አብረው እየሰሩ መሆኑን፣
- የወልቂጤ ከተማ በፕሮጀክቱ ላይ በተፈጠሩት ችግሮች ላይ በስልክና በአካል በመሄድ የመፍትሄ አቅጣጫ በማስቀመጥ የምክር አገልግሎት እንደሚሰጠውና ውይይት እንደተደረገ፣

ገልጸዋል፡፡

61. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ የፕሮጀክት ጥናትና አዋጭነቱ የተገመገመው ዕውቅና ባለው አማካሪ ድርጅት ቢሆንም ጽ/ቤቱ ብድር ከመስጠቱ በፊት በቂ የሆነ ዝርዝር የአዋጭነት ግምገማ ማካሄድ የሚገባው በመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

62. ጽ/ቤቱ ለብድር ጥያቄ የሚቀርቡ ጥናቶች አዋጭ እና ወቅታዊ መሆናቸውን ቅድመ ግምገማ የማያደርግና አስፈላጊውን መረጃዎች በማየት ብድር የማይሰጥ ከሆነ በብድር አመላለሱ ላይ ተፅዕኖ ከመፍጠሩም በላይ የሀገር ሀብት እንዲባክን ሊያደርግ ይችላል፡፡

ብድር ፈላጊዎች ወቅታዊ Business Plan, Feasibility study and Detail desig እንዲሁም ዋስትና ያቀረቡ መሆኑን በተመለከተ፣

63. ጽ/ቤቱ ብድር ፈላጊዎች ከፈንዱ ለመበደር ጥያቄ ሲያቀርቡ ወቅታዊ የቢዝነስ ዕቅድ (Business Plan)፣ የአዋጭነት ጥናት(Feasibility study)፣ ዝርዝር የዲዛይን ጥናት (Detail design) እና ከክልሉ የተሰጣቸውን የዋስትና ሰነዶች ሊያቀርቡ ይገባል፡፡ ጽ/ቤቱም የቀረቡትን ሰነዶች በመገምገም ብድር ሊሰጥ ይገባል፡፡

64. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱት ማስረጃዎች፡-

    - ከ20 ከተሞች ውስጥ የ6 ከተሞች (ለገጣፎ፣ በደኖ፣ያቤሎ፣ ጭንቻ፣ ወራቤ፣ ጋምቤላ ከተሞች) የቢዝነስ ዕቅድ፣ የአዋጭነት ጥናት እና ዝርዝር ዲዛይን የጥናት ሰነድ ሳይኖራቸው ብድር የወሰዱ መሆኑ፣

- የሚዛን፣ ሐረር፣ ሊሙ-ገነት፣ ዱራሜ፣ ገንዳውሃ፣ ቡራዩ፣ ባሌሮቤ፣ ፊንጫ፣ ሰንዳፋ፣ ሀሰሳ፣ ጎቤሳ፣ ቦዲቲ፣ ተርጫ፣ አቢአዲ፣ ሰቆጣና ባምቢስ ከተሞች የአዋጭነት ጥናት (Feasibility Study) ሳያቀርቡ ብድር የተሰጣቸው መሆኑ፣
- የክብረመንግስት፣ ሀረር፣ ባሌ ሮቤ፣ ፊንጫ፣ ሰንዳፋ፣ ሀሰሳ፣ ስሬ፣ ሳውላ፣ ተርጫ፣ አቢአዲ፣ ሰቆጣና ባምቢስ ከተሞች የቢዝነስ ዕቅድ(Business plan) ሳይኖራቸው ብድር የወሰዱ መሆኑ፤
- ሐረር፣ ሳውላ፣ ዝርዝር ዲዛይን (Detail design) ሳይኖራቸው ብድር የወሰዱ መሆኑ፤
- ሚዛን፣ ክብረ መንግስት፣ ሐረር፣ ገንዳ ውሃና ሽሬ-እንዳስላሴ የተጠናው ጥናት ተገምግሞ የግምገማ ሪፖርት (Appraisal Report) ሳይኖራቸው ብድር የወሰዱ መሆኑ፤

  ክልሎች ለከተሞች ውሃና ፍሳሽ ተቋም የብድር ዋስትና የገቡበትን ማስረጃ ጽ/ቤቱ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ከ28 ከተሞች በስተቀር የሌሎቹን የ37 ከተሞች ማስረጃ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ሊቀርብ አለመቻሉን፣ (ዝርዝሩ በአባሪ 7 ተያይዟል)

ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ተጠይቀው በሰጡት አስተያየት፡-

- የ6 ከተሞች የጥናት ሰነድ የሚያስፈልገውን መረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት ፕሮጀክቱ እንደገና ጥናት እንዲጀምር ከግምገማ ቡድኑ እና ከቦርድ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ለፕሮጀክት ማስጠኛ የሚሆን ገንዘብ ብድር እንደተሰጠ፣
- የሚዛን፣ ክብረ-መንግስትና ሀረር የአዋጭነት ጥናት (Feasibility Study)ና የፕሮጀክት ግምገማ ሪፖርት (Appraisal Report) ቀደም ብለው የተሰሩ ፕሮጀክቶች ስለሆኑ ሰነዳቸውን ማግኘት አለመቻላቸው፤ የቀሪዎቹ ሰነዶች ግን እንዳለና እንደሚቀርቡ መግለጻቸው፤
- የክብረመንግስት፣ ሚዛን-አማን፣ ሀረር፣ ወልቂጤ፣ አክሱም፣ አሶሳና አዲስ አበባ ቀደም ብሎ የብድር ዋስትና ደብዳቤያቸው ለጽ/ቤቱ የመጣ በመሆኑና ከመዘግየቱ የተነሳ በየትኛው ፋይል እንደተቀመጠ ማስታወስ ባለመቻሉ ሊቀርብ እንዳልተቻለና የቀሪዎቹ 29 ፕሮጀክቶች የብድር ዋስትና የሚመለከታቸውን ክልሎች እንዲቀርብ በደብዳቤ መጠየቃቸውን፣

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

66. የጽ/ቤቱ ኃላፊ የቀሪዎቹ 29 ፕሮጀክቶች የብድር ዋስትና የሚመለከታቸውን ክልሎች እንዲቀርብ በደብዳቤ መጠየቃቸውን፣ ቀሪዎቹ ሰነዶች እንደሚቀርቡና የገለጹ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ደርስ አለ የተባለው ማስረጃ ሊቀርብ ያልቻለ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል አልቻልንም፡፡

67. ጽ/ቤቱ የብድር ጥያቄዎችን በሚቀበልበት ጊዜ የጥናት ሰነዶቹ የተሟሉና ወቅታዊ አለመሆናቸው እንዲሁም የክልል መቅረብ ያለበት ዋስትና አለመቅረቡ ከፕሮጀክት ግንባታ ጋር ተያይዞ ፕሮጀክቱ በታቀደለት ጊዜና በሚፈለገው መጠን ተጠናቆ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት እንዳይሰጥ ከማድረጉም በላይ በብድር የተሰጠው ገንዘብ ወቅቱን ጠብቆ እንዳይመለስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን የክትትል እና የግምገማ ሥራዎች በተመለከተ፣

68. ጽ/ቤቱ በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜና ገንዘብ እንዲያልቁ እና ለታለመላቸው ዓላማ የዋሉ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ እንዲችል በአመታዊ እቅድ በመያዝ የክትትልና የግምገማ ሥራዎችን ሊሰራ ይገባል፡፡

69. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ጽ/ቤቱ በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እየተከናወኑ እና ለታለመላቸው ዓላማ እየዋሉ ስለመሆኑ የክትትል እና የግምገማ ሥራዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረተ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ የማያከናወን መሆኑ፡-
- ጥር 21 ቀን 2016 ሽሬ እንዳ ስላሴ፣ አጣየ፣ ኬሚሴ፣ መርሳ፣ ሸዋ-ሮቢት፣ ወረኢሉ ፊቼ እና ገብረ ጉራቻ፣ በግንቦት 16 ቀን 2016 ሃዋሳ፣ ቡታጂራ፣ ሆሳዕና፣ ደምቢዶሎ እና ወላይታ ሶዶ፣ ታህሳስ 7 ቀን 2015 ሆለታ የመስክ ምልከታ እንደተደረገ የሚገልጽ ማስረጃ የቀረበ ሲሆን፤ የቀሪዎቹ 48 ከተሞች ክትትል ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

70. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው ሲመልሱ የመስክ ምልከታ ሪፖርት በተገቢው የሰነድ አያያዝ እና ሪፖርቲንግ ሲስተም በተጠናከረ ሁኔታ የተጀመረው ከባለፈው 2008 ዓ.ም ጀምሮ እንደሆነና ቀደም ብለው የተሰሩት የመስክ ምልከታዎች የሪፖርት ሰነዶች ማግኘት ባለመቻሉ ሊቀርብ እንዳልቻለ ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

71. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ ከ2008 ዓ.ም በፊት የክትትልና ግምገማ ሥራ ስለመሰራቱ የሚገልጹ ማስረጃዎች ያልቀረቡና በ2008 ዓ.ም ተሰሩ ከተባሉት

ውስጥም የ48 ከተሞች ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

72. ፕሮጀክቱ ተጀምሮ እስከሚያልቅና ርክክብ እስከሚደረግ ድረስ በዕቅድ ላይ በተመሰረተ መልኩ የፕሮጀክት ክትትልና ግምገማ ባለመደረጉ በፕሮጀክቱ ላይ በየጊዜው የሚከሰተውን ችግር በወቅቱ የመፍትሄ አቅጣጫ ለመስጠት የማያስችል ከመሆኑም በላይ ለፕሮጀክቱ በተያዘለት በጀትና ጊዜ ተጠናቆ ለተጠቃሚው አገልግሎት እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ጽ/ቤቱ ባስቀመጠው ያገልግሎት ስታንዳርድ መሠረት ብድር እየሰጠ ስለመሆኑ፣

73. ጽ/ቤቱ የሚሰጠውን ብድር በተመለከተ ባስቀመጠው ያገልግሎት ስታንዳርድ መሠረት መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

74. ጽ/ቤቱ የሚሰጠውን ብድር ባስቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ መሠረት ሊሰጥ እንደሚገባ በጽ/ቤቱ መዋቅር ላይ የተገለጸ ቢሆንም በፕሮጀክት ግምገማና ክፍያ ሂደት ላይ የመዘግየት እንዲሁም ይሁንታ /NO objection/ ሲሰጥ ባስቀመጠው ያገልግሎት ስታንዳርድ መሰረት የማይሰጥ መሆኑን በናሙና መርጠን ባየናቸው ተበዳሪ ከተሞችና ባለድርሻ አካላት የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

75. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው ቀደም ብሎ በነበሩት የይሁንታ አሰጣጥ መጓተት እንደነበረና በአሁን ጊዜ ግን የተሻለ የይሁንታ አሰጣጥ ላይ እንዳለ ነገር ግን የጽ/ቤቱ የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን አገልግሎቱ የሚሰጠው አካል (ተበዳሪ ከተማ፣ አስፈጻሚ የቢሮዎች፣ ክፍያ የሚፈጸምባቸው አካላት) ሊያሟሉ የሚገባቸውን አሟልተው ሲቀርቡ የተሻለ የይሁንታ አሰጣጥ እንደሚኖር በነባራዊ ሁኔታ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

76. ጽህፈት ቤቱ ለተገልጋዮችና ለባለድርሻ አካላት ባስቀመጠው ያገልግሎት እስታንዳርድ መሠረት ስራዎችን ባለመስራቱ ከክፍያና ግዥ ጋር ተያይዞ መጉላላትን ሊፈጥር የሚችል ሲሆን በተጨማሪም ፕሮጀክቱ ማለቅ ከሚገባው ግዜ እንዲዘገይ አስተዋጽዎ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2.3 ጽሕፈት ቤቱ ከፈጻሚ ባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋና ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ

የጽ/ቤቱ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

77. የጽ/ቤቱ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ መረጃዎች አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

78. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጽ/ቤቱ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ ማስረጃዎች አያያዝ፣

- በክፍያ ሰነዶች ላይ የመረጃ አያያዝ ችግር በመኖሩ የክፍያ መጓተት፤
- የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም መረጃዎች፣ ለክትትልና ግብረ መልስ ስራዎች በአግባቡ ያለመቀበል እና አደራጅቶ የመያዝ፣ ችግሮች መኖራቸው፣
- ጽ/ቤቱ የአዋጭነት ጥናት (Feasibility Study) እና የፕሮጀክት ግምገማ ሪፖርት (Appraisal report) ሰነዶች አያያዝ ችግር ስላለበት የሚዛን፣ የክብረ መንገስት እና የሀረር ከተሞች ላይ የተከናወኑትን ማግኘት አለመቻላቸው፣
- የክብረመንግስት፣ ሚዛን-አማን፣ ሀረር፣ ወልቂጤ፣ አክሱም፣ አሶሳና አዲስ አበባ የብድር ዋስትና ያስያዙበት መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

79. ስለሁኔታው የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠይቀው

- ጽ/ቤቱ ቀደም ሲል በተደጋጋሚ የቢሮ ለውጦች ከማድረጉና ከመዋቅሩ ጥበት ጋር ተያይዞ ስራውን በትክክል ሙያዊ አካሄድ ሊመራና ምክር ሊሰጥ የሚችል ባለሙያ ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና ልውውጥ ሥርዓት ያልተዘረጋ ሲሆን ወደፊት ለመዘርጋት እንዳቀዱ፣
- የከተሞች ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅቶች በኩል ተደጋጋሚ የኃላፊዎች መለዋወጥ በመኖሩ የተጠቀሰው ችግር እንዳለ እንዳወቁና የተፈለጉ ሰነዶችን በድጋሚ ኮፒ በማድረግ እየሰጡ እንደሚገኙ፣
- የክብረመንግስት፣ ሚዛን-አማን፣ ሀረር፣ ወልቂጤ፣ አክሱም፣ አሶሳና አዲስ አበባ ቀደም ብሎ የብድር ዋስትና ደብዳቤያቸው ለጽ/ቤቱ የመጣ በመሆኑና ከመዘግየቱ የተነሳ በየትኛው ፋይል እንደተቀመጠ ማስታወስ ባለመቻሉ ሊቀርብ እንዳልተቻለ፣

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

80. ጽ/ቤቱ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና ልውውጥ ሥርዓት ባለመዘርጋቱና ማስረጃዎቹ ባለመያዛቸው የመረጃ መጥፋት፣ መረጃዎች ለተጠቃሚዎች በወቅቱ እንዳይደርሱ ከማድረጉም በላይ የፋይናንስና ብድር አስተዳደሩን አደጋ ላይ ሊጥለው ከመቻሉም በላይ ለፖሊሲ ውሳኔ ሚፈለጉ መረጃዎች በቀላሉ እንዳይኙ ያደርጋል፡፡

ጽ/ቤቱ ስለሚያከናውናቸው ሥራዎች ለተበዳሪዎች እና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ የሰራ ስለመሆኑ፣

81. ጽ/ቤቱ ወጪን ማስመለስ መርሆ እና የተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀምን በተመለከተ ለተበዳሪዎች (ለከተማ መስተዳድሮች፣ የውሃ አገልግሎት ተቋም እና የመስኖ ማህበራት) እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ ይገባል፤

82. ይሁን እንጂ የጽ/ቤቱ ቦርድ አመራር ጽ/ቤቱ ከተሞች የወሰዱትን ብድር በገቡት ስምምነት መሰረት መመለስ እንዲችሉ በጀት በመያዝ ተገቢውን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እንዲከናወን በቀን12/01/2003 ዓ.ም በተደረገ ስብሰባ (በቦርድ ቃለ-ጉባኤ ቁጥር 57) ውሳኔ ያሳለፈ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩት የከተሞች ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋም የስራ ኃላፊዎች ጽ/ቤቱ ስለ ወጪ ማስመለስ መርሆ፣ የተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀም እና የጽ/ቤቱን ሥራ በተመለከተ ሙያዊ የምክር አገልግሎት እና የፈንድ አጠቃቀም ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ እንዳልተሰጣቸው ገልጸዋል፡፡

83. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት የጽህፈት ቤቱ መዋቅር ጠባብ በመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችና ሙያዊ ድጋፍ አለመስጠታቸውን ገልጸዋል፡፡

84. የጽ/ቤቱን ተልዕኮ፣ ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም የብድር አስተዳደር ሥርዓት እና የወጪ ማስመለስ መርህ ላይ በተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ተከታታይነት ባለው መልኩ ግንዛቤ አለመፍጠሩ የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማቱ ስለውሃ ልማት ፈንድ ግንዛቤ እንዳይኖራቸውና የወሰዱትንም ብድር በተፈለገው ጊዜ እንዳልመለሱ እንዲሁም ተቋማቱ ከውሃ ልማት ፈንድ የሚሰጠውን አገልግሎት እንዳያገኙ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል፡፡

የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ ዘመናዊ በሆነ የመረጃ ቴክኖሎጂ ተደግፎ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠቱን በተመለከተ፤

85. የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ ዘመናዊ በሆነና በተጠናከረ የመረጃ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ አስተማማኝና የተቀላጠፈ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡

86. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡- የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ አስተዳደር ዘመናዊ በሆነና በተጠናከረ የመረጃ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑ፣ እና የ2007ና የ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ ለብድር ሂሳብ ምዝገባ አገልግሎት የሚውል ሶፍትዌር ዝግጅትን እና የኔትወርክ ዝርጋታ ስራ ሙሉ ለሙሉ (100 ፐርሰንት) ለማጠናቀቅ ታቅዶ ያልተከናወነ መሆኑ፣ ስለዚህ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሚሰበሰበው ገንዘብ ወጥነት ያለው ሶፍትዌር ስለሌለ የየፕሮጀክቶቹ የገቢና ወጪ ሂሳብ በተናጠል በተለያዩ ኮፒዩተሮች የሚመዘገብ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

87. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፡-

- ለብድር ሂሳብና አስተዳደር ሶፍትዌር (LAAS) አገልግሎት እንዲውል የተዘጋጀው ሶፍትዌር ስራ በኮንትራቱ አፈጻጸም በኩል ባጋጠመው አንዳንድ ችግሮች የተነሳ እንደታሰበው ስራው ያልተጠናቀቀ ቢሆንም ያሉት ኮንትራታዊ ችግሮች የሚፈቱበት መንገድ እየተመቻቸ በመሆኑ ስራው በቅርቡ እንደሚጠናቀቅ፣ የኔትወርክ ዝርጋታው ስራ በተጨማሪዎቹ የቢሮዎች ግንባታ ስራ ባለመጠናቀቁ ምክንያት እንደታሰበው ዕቅዱ ሊፈጸም እዳልቻለ፣
- የተጠቀሰው ሶፍትዌር ባለመጠናቀቁ የፕሮጀክት ገቢና ወጪው በተለያዩ ባለሙያዎችና ኮምፒዩተሮች በተናጠል እየተመዘገቡ እንደሚገኙና የተጀመረው የሶፍትዌር ሥራ ሲጠናቀቅ ወይም ደግሞ የተሻለ ሶፍትዌር ሊገኝ/ሊዘጋጅ የሚችልበት መንገድ ከተገኘ ችግሩ ሊቃለል እንደሚችል፣

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

88. ጽ/ቤቱ በተሟላ እና በዘመናዊ መልኩ የብድር ሂሳቡን አለማደራጀቱ አገልግሎቶቹን በቅልጥፍናና እንዳይሰጥ እና የብድር ሂሳብ አመዘጋገቡን አስቸጋሪና ለተገልጋዬች የተቀላጠፈ የፋይናንስ አገልግሎት እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የጽ/ቤቱን የተለያዩ መረጃዎች ለባለድርሻ አካላትና ተጠቃሚዎች ለማድረስ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ስለመኖሩ፣

89. የጽ/ቤቱን የተለያዩ መረጃዎች ለባለድርሻ አካላትና የተለያዩ ተጠቃሚዎች እንዲደርስ ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ድረ-ገፅ (ዌብ ሳይት) መዘርጋት አለበት፡፡ እንዲሁም የፈንድ ማመንጨትና ብድር አስተዳደርን የሚመለከቱ በተለያየ ጊዜ የወጡትን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ለተበዳሪ ተቋማትና ባለድርሻ አካላት መረጃዎችን ሊያሰራጭ ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ጽ/ቤቱ የተለያዩ መረጃዎች ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት (ዌብ ሳይት) የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማትና ለባለድርሻ አካላት የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የጽ/ቤቱ አዋጅና ከውሃ ልማት ፈንድ አሰራር ጋር የተያያዙ መመሪያዎች ያልደረሳቸው መሆኑ ለመረዳት/ለማወቅ/ ተችሏል፡፡

91. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው የጽህፈት ቤቱ መዋቅር ጠባብ በመሆኑ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ አገልግሎት የሚሰጥ ዌብሳይት በውጭ ባለሙያዎች እንዲዘጋጅ ለማድረግ የሚያስችል የሰው ኃይል ባለመኖሩ እስካሁን ድረስ ዌብ-ሳይቱ ያልተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም መመሪያና አዋጅ እንዲደርሳቸው ባይደረግም የፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማ በሚደረግበት ጊዜና በብድር ስምምነት ወቅት ስለጽ/ቤቱ በግልጽ እንዲያውቁት እንደሚደረግ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (fact sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

92. ጽህፈት ቤቱ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ አገልግሎት አለመዘርጋቱ የጽህፈት ቤቱ ሥራዎችና የሚሰራባቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ለባለድርሻ አካላት እና ለውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማት እንዲደርስና እንዲያውቁት ባለመደረጉ ጽ/ቤቱ የተቋቋመበትን ዓላማና የሚያከናውናቸውን ተግባራት እንዲረዱትና ስለጽ/ቤቱ የብድር አስተዳደር በግልጽ አውቀው እንዳይሰሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የጽ/ቤቱን ስራ በተመለከተ ከተገልጋዮች እና ከባለድርሻ አካላትጋር የውይይት መድረክ ስለመኖሩ፣

93. የጽ/ቤቱን ሥራ በተመለከተ ከተገልጋዮች፣ ከአስፈጻሚ እና ከባለድርሻ አካላትጋር በየዓመቱ የውይይት መድረክ ሊዘጋጅና በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

94. ይሁን እንጂ የጽ/ቤቱን ሥራ በተመለከተ ከተገልጋዮችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በየዓመቱ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በብድር አቅርቦት፣ አፈጻጸማቸው እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ውይይት ለማድረግ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም በዕቅዱ መሰረት ያልተከናወነ እና በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የየከተሞቹ የውሃ አገልግሎቶች እና የክልል የውሃ ቢሮዎች መድረኩ ስለመኖሩ የማያውቁ መሆናቸውን ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

95. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በጽህፈት ቤቱ በኩል የተሰጡ አስተያየትና ማብራሪያዎች እንዳሉ ሆነው ለጽ/ቤቱ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ብድር

ከወሰዱና ብድር መመለስ ለጀመሩ የውሃ አገልግሎት ተቋማት ጋር በተያዘው በጀት ዓመት የውይይትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለማከናወን እንዳቀዱ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል፡፡

96. ጽ/ቤቱ ስለ ወጪ ማስመለስ መርሆ፣ የተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀም እና የጽ/ቤቱን ሥራ በተመለከተ የተከናወኑ ስራዎች ዕቅድ እና አፈጻጸም ላይ ፣ ሙያዊ የምክር አገልግሎት እና ግንዛቤ ማስጨበጫ ከተገልጋዮችና ለባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በቅንጅትና በትብብር አለመስራቱ ሁሉም ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት የመጠጥ፣ የሳኔቴሽን እና የመስኖ ሥራዎች ወጥ በሆነ እቅድ እንዳይፈጽሙ እና የሚጋጥሙ ችግሮች በጽፍጥነት እንዳይፈቱና ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

ክፍል ሶስት

መደምደሚያ

97. የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት ለንፁህ መጠጥ ውሃ፣ ሳኒቴሽን እና ለመስኖ ልማት ከተለያዩ ፋይናንሰሮች የሚሰበስበው ገንዘብ በአግባቡ ለሚፈለገው ዓላማ መዋሉን፣ የብድር አስተዳደሩ በፍትሃዊነት ለሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ክፍፍል የሚደረግበትን ሁኔታ በማመቻቸት ይኖርበታል፡፡ ይህንን ዓላማውን ለማሳካት እና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ ፈንድ ማመንጨትና ብድር አስተዳደር ውጤታማና አስተማማኝ በሆነ መንገድ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት ዓላማውን ለማሳካት የቻለና ውጤታማ ስለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና የአሰራር ግድፈቶች እና ክፍተቶች ተገኝተዋል፡፡

- ጽ/ቤቱ በዜጎች ቻርተሩ መሰረት ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት የፕሮጀክት ፕሮፋይል አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ያላቀረበና ለዚህ አገልግሎት የሚሆን ፋይናንስ የማፈላለግ ሥራ ያልሰራ መሆኑ፤
- የጽ/ቤቱን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን ያላስጠና መሆኑ፤
- ጽ/ቤቱ ከተለያዩ ምንጮች ለፈንዱ የሚሰበስበውን ገንዘብ ትክክለኛ እና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብትን ከደጋፊ ሰነዶች ጋር በመያዝ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ በወቅቱ በትክክል የማይመዘገብ እና የፈንዱ ሂሣቡን በወቅቱ የማይዘጋ መሆኑ፣
- ጽ/ቤቱ የፈንዱ ሂሣብ በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት ተደርጎ የማያውቅ መሆኑ፤
- ጽ/ቤቱ በቦርድ ባልጸደቀ የብድር አሰጣጥ ረቂቅ መመሪያ ብድር እየሰጠ መሆኑ፣
- ጽህፈት ቤቱ ለብድር ተጠቃሚ ከተሞች መምረጫ የሚያገለግል መመሪያ ያላዘጋጀ መሆኑ፤
- ጽ/ቤቱ ለሁሉም ተበዳሪዎች ለሚሰበስበው የፕሮጀክት መዋጮ (Matching Fund) የብድሩን መጠን ስንት መቶኛ(ፐርሰንት) ማዋጣት እንደሚገባቸው የሚወስን ግልጽ መስፈርት ያልተዘጋጀ መሆኑ እና ተበዳሪ ተቋማት የፕሮጀክት መዋጮ እንዲያዋጡ የማይደረግና ማዋጣት ከጀመሩትም በወቅቱ የማይሰበሰብ መሆኑ፤

❖ ከጽ/ቤቱ ቅድሚያ ብድር አግኝተው ከተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ውስጥ ያልተሰበሰበ የብድር ተመላሽና ወለድ በድምሩ ብር 111,954,101.70 (አንድ መቶ አስራ አንድ ሚልዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሣ አራት ሺህ አንድ መቶ አንድ ብር ከሰባ ሳንቲም) ያልሰበሰበ መሆኑ፤ ለቆጋ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ የዋለው 37.84 ሚልዮን ዩሮ ወጪ እና ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ የቆየ ቢሆንም የብድር ተመላሹ መሰብሰብ ያልተጀመረ መሆኑን፣

❖ ጽ/ቤቱ ከከተሞች ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ጋር በገባው የብድር ውል ስምምነት መሰረት በወቅቱ ብድር በማይከፍሉ ተበዳሪ ከተሞች ላይ በብድር ውሉ መሰረት የተጨማሪ የወለድ ወለድ ቅጣት የማያስከፍል መሆኑ

❖ በናሙና ከታዩ ለጽ/ቤቱ ከቀረቡ የብድር ጥያቄዎች ውስጥ በቅድሚያ የጥናት ሰነዶቹ ወቅታዊና አዋጭ መሆናቸው ሳያረጋግጥ ለ5 ከተሞች ብድር የተሰጠ መሆኑ፤ ከጽ/ቤቱ ብድር ወስደው ወቅታዊ የጥናት ሰነድ ማቅረባቸውን ለማረጋገጥ ሲታይ ወቅታዊ የቢዝነስ ዕቅድ፣ የአዋጭነት ጥናት እና ዝርዝር ዲዛይን (Business Plan, Feasibility study and Detail design) ሳያቀርቡ ለተወሰኑ ከተሞች ብድር የሰጠ መሆኑ፤

❖ ጽ/ቤቱ በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እየተከናወኑ እና ለታለመላቸው ዓላማ እየዋሉ ስለመሆኑ የክትትል እና የግምገማ ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ የማይከናወን መሆኑ፡ ጽ/ቤቱ የሚሰጠው ይሁንታ (No objection) እና የክፍያ ሂደት ባስቀመጠው የአገልግሎት አሰጣጥ እስታንዳርድ መሰረት የማይሰጥ መሆኑ፤

❖ ጽ/ቤቱ ዘመናዊ የሆነ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ ማስረጃዎች አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤

❖ ጽ/ቤቱ ስለ ወጪ ማስመለስ መርሆ፣ የተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀም እና የጽ/ቤቱን ሥራ በተመለከተ ሙያዊ የምክር አገልግሎት እና የፈንድ አጠቃቀም ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ ያልሰጠ መሆኑ፤

❖ የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ አስተዳደር ዘመናዊ በሆነና በተጠናከረ የመረጃ ቴክኖሎጂ የማይጠቀም መሆኑ፤

❖ ጽ/ቤቱ የተለያዩ መረጃዎች ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ድህረ-ገጽ (ዌብ ሳይት) የሌለው መሆኑ፤

- የጽ/ቤቱን ሥራ በተመለከተ ከተገልጋዮች፣ ከአስፈጻሚዎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በየዓመቱ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በብድር አቅርቦት፣ አፈጻጸማቸው እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ውይይት የማያደርግ መሆኑ፡፡

98. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሃሳቦች

99. ጽ/ቤቱ ፈንድ ማመንጨትና ብድር አስተዳደር በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና አስተማማኝ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው አቅርበናል፡-

- ❖ ጽ/ቤቱ በዜጎች ቻርተሩ ላይ ለመተግበር ቃል በገባው መሰረት የረዥም ጊዜ ብድር ለከተሞቹ እና የመስኖ ማህበራት ለሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት ፕሮጀክት ወጭን በማስመለስ መርሆ ላይ ተመስርቶ ለመስጠት እንዲችል አስፈላጊ የሆኑ አጋዥ ደንብ እና መመሪያዎች በማዘጋጀት እና በሚመለከታቸው አካላት በማጸደቅ የፕሮጀክት ፕሮፋይል እያዘጋጀ እና በቦርዱ እያጸደቀ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡
- ❖ የጽ/ቤቱን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በማጥናት ወይም በማስጠናት ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በማጸደቅ የፈንዱን ገቢ ሊያሳድግ ይገባል፡፡
- ❖ ጽ/ቤቱ ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስበውን የፈንዱን ገንዘብ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት በወቅቱ ተከታትሎ ሊመዘግብና ሂሣቡን በወቅቱ ሊዘጋ ይገባል፡፡
- ❖ ፈንዱ ከተቋቋመ ጀምሮ ኦዲት ባለመደረጉ አስፈላጊ ምዝገባዎችን እና ሰነዶችን በማዘጋጀት በፍጥነት የፈንዱ ሂሳብ በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት ሊደረግ እና ሪፖርቱ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት ሊደረግ ይገባል፡፡ በቀረቡት ሪፖርቶች መሰረትም ተገቢ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ መደረግ አለበት፡፡
- ❖ ጽ/ቤቱ በአዋጅ 268/1994 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 በተደነገገው መሰረት ተዘጋጅቶ በረቂቅ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛ መመሪያ የሚመለከታቸውን አካላት በማወያየት እና ለቦርዱ አቅርቦ በማጸደቅ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በተጨማሪም ጽ/ቤቱ የብድር ተጠቃሚ የሚሆኑ ከተሞችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልፅ የሆነ የከተሞች መምረጫ መስፈርት መመርያ አዘጋጅቶና አጸድቆ ተግባራዊ በማድረግ የብድር አሰጣጡ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ጽ/ቤቱ ከሁሉም ተበዳሪዎች ለሚሰበስበው የፕሮጀክት መዋጮ (Matching Fund) የብድሩን መጠን ስንት መቶኛ(ፐርሰንት) ማዋጣት እንደሚገባቸው የሚወስን ግልጽ መስፈርት በማዘጋጀትና በሚመለከተው አካል አጸድቆ ተግባራዊ በማድረግ ሊያስከፍልና በወቅቱ መሰብሰብ አለበት፡፡ ተበዳሪ ተቋማት የወሰዱትን ብድር በወቅቱ የማይከፈሉ ከሆነ ጽ/ቤቱ በውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት ሊፈጽም እና የወለድ ወለድ ሊቀጣ ይገባል፡፡
- ለጽ/ቤቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎች በቅድሚያ የጥናት ሰነዶቹ ወቅታዊና አዋጭ መሆናቸው ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ስለዚህ ጽ/ቤቱ ለብድር ፈላጊዎች ብድር ከመስጠቱ በፊት ወቅታዊ የቢዝነስ ዕቅድ፣ የአዋጭነት ጥናት እና ዝርዝር የዲዛይን ጥናት (Business Plan, Feasibility study and Detail desig) ሰነዶች ተሟልተው የቀረቡ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ጽ/ቤቱ በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ተጀምረው ርክክብ እስከሚደረግላቸው ጊዜ ድረስ በታቀደላቸው ጊዜና ገንዘብ እንዲያልቁ እና ለታለመላቸው ዓላማ የዋሉ ስለመሆናቸው እቅድ በመያዝ የክትትልና የግምገማ ሥራዎች ሊሰራ ይገባል፡፡
- ጽ/ቤቱ የሚሰጠው ይሁንታ (No objection) ና የክፍያ ሂደት ባስቀመጠው ያገልግሎት እስታንዳርድ መሠረት ሊሰጥ ይገባል፡፡
- የጽ/ቤቱ ዘመናዊ የሆነ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ የጽ/ቤቱ የብድር ፋይናንስ ዘመናዊ በሆነና በተጠናከረ የመረጃ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ አስተማማኝና የተቀላጠፈ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ የጽ/ቤቱን የተለያዩ መረጃዎች አደራጅቶ በመያዝ ለተለያዩ ተጠቃሚዎችና ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ለማድረግ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ድረ-ገፅ (ዌብ ሳይት) ሊጠቀም ይገባል፡፡ በጅምር ላይ ያሉና የተንጓተቱ ዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂዎችም በፍጥነት ተጠናቀው ወደ ሥራ የሚሸጋገሩበት ሁኔታ ጽ/ቤቱ ማመቻቸት አለበት፡፡
- ጽ/ቤቱ ስለ ወጪ ማስመለስ መርሆ፣ የተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀም እና የጽ/ቤቱን ሥራ በተመለከተ ሙያዊ የምክር አገልግሎት እና የፈንድ አጠቃቀም ላይ እቅድ በመያዝ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ለተበዳሪ ተቋማትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ሊሰጥ ይገባል፡፡

- የጽ/ቤቱን ስራ በተመለከተ ከተገልጋዮች፣ ከአስፈጻሚዎች እና ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ጋር ቢያንስ በየዓመቱ በያሚያቅዳቸው እቅዶች ሆነ በዕቅድ አፈጻጸሙ ላይ የውይይት መድረክ ሊያዘጋጅ ስራዎችን ሊገመግም እና በቅንጅት ሥራዎች የሚሰሩበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት፣ የጽ/ቤቱ ባለድርሻ አካላትና በናሙና የታዩ የጽ/ቤቱ ተበዳሪ የከተሞችና ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋም የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ 1፡ የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት ድርጅታዊ መዋቅር



አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ	የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች
I. ጽ/ቤቱ ፈንድ ማመንጨት ሂደት ለማከናወን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም	1. ጽ/ቤቱ ስለፈንዱ አሰባሰብ የአሰራር ሥርዓት መመርያ አውጥቶ በቦርድ ሊያጸድቅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	2. በጽ/ቤቱ የወጡትን መመርያዎች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊያሰራጭ ይገባል፡፡
	3. ጽ/ቤቱ ከቦርድ ጋር በመሆን ለውሃ አቅርቦት፣ ሳኒቴሽን እና የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል/ፕሮፋይል/ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማቅረብና ክትትል በማድረግ ፋይናንስ ሊያፈላልግ ይገባል፡፡
	4. ጽ/ቤቱ ፈንድ ለመሰብሰብና ብድር ለማቅረብ የሚያስችል ስትራቴጂክ እቅድ ሊኖረው ይገባል፡፡ ስትራቴጂክ እቅዱም ከእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ጋር የተጣጣመ ሊሆን ይገባል፡፡
	5. ጽ/ቤቱ በተዘጋጀው ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ በየአመቱ መንዝሮ በማቀድ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
	6. የጽ/ቤቱን የተዘዋዋሪ ፈንድ ክምችት ለማጠናከር የሚረዱ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዘዴዎችን በማስጠናት በሚመለከተው አካል ሊያጸቅና ሊተገበር ይገባል፡፡
	7. 7.ጽ/ቤቱ ለፈንዱ መግባት የሚገባውን ከተለያዩ ምንጮች የሚገኘውን ገንዘብ ሁሉ በወቅቱ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡
	8. ጽ/ቤቱ ከተለያዩ ፈንድ አቅራቢዎች፣ ከመንግስት፣ ከብድር ተመላሽ እና ከፕሮጀክት መዋጮ ለሚሰበሰበው ገንዘብ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት ተከትሎ በወቅቱ ሊመዘገብ ይገባል፡፡
	9. ጽ/ቤቱ የፈንዱን ሂሣብ በውጭ ኦዲተሮች በያመቱ ኦዲት ሊያስደርግ ይገባል፡፡
	10. ለጽ/ቤቱ የቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶችን በመገምገም በተሰጡት አስተያየቶች መሰረት ተገቢ እርምጃዎች የተወሰዱ መሆኑ በየደረጃው መረጋገጥ አለበት፡፡
II. ጽ/ቤቱ የብድር አስተዳደር ቀልጣፋና	11. ጽ/ቤቱ የብድር አሰጣጥና አወሳሰን መመዘኛ መመርያና መስፈርት አውጥቶ በቦርድ በማጸደቅ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ	የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች
ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ያደረገ መሆኑ መገምገም	12. ጽ/ቤቱ ለውሃ አቅርቦት፣ ሳኒቴሽን እና ለመስኖ ልማት ሥራ አገልግሎት የሚሆን ቦርዱ ባጸደቀው የብድር አሰጣጥ መመዘኛ መሠረት በየመቱ የሚቀርቡ የብድር ጥያቄዎችን በመገምገም ለተበዳሪዎች ብድር መስጠት አለበት፡፡ይኖርበታል፡፡
	13. ጽ/ቤቱ ለውሃ አቅርቦት፣ ሳኒቴሽንና ለመስኖ ልማት ዓላማዎች እውን ለማድረግ ወጪን በማስመለስ መርሆ ላይ የተመሰረተ የብድር ውል ስምምነት በመዋዋል የረጅም ጊዜ ብድር ማበደር አለበት፡፡
	14. በብድር ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ከተበዳሪ ተቋም የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ (Matching Fund) በወቅቱ ሊሰበሰብ ይገባል፡፡
	15. ጽ/ቤቱ ከተበዳሪዎች መሰብሰብ የሚገባውን የብድር ተመላሽና ወለድ የሚመለሱበት መርሀግብር ተዘጋጅቶ በወቅቱ እና በወጣው በመረሀ ግብር መሠረት ሊሰበሰብ ይገባል፡፡
	16. ጽ/ቤቱ በመርሀ-ግብሩ መሰረት በወቅቱ ያልተሰበሰበ ብድር ሲኖር በውሉ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡
	17. ጽ/ቤቱ የፕሮጀክት አዋጭነት ግምገማ መመርያ ሊያወጣና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	18. ጽ/ቤቱ ለብድር ጥያቄ የሚቀርቡ ጥናቶች አዋጭ መሆናቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
	19. ከፈንዱ ብድር ተጠቃሚ ለመሆን ብድር ፈላጊ ተቋም በአዋጅ የተቋቋመና ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሊሆን ይገባል፡፡
	20. ብድር ፈላጊዎች ለመበደር ወቅታዊ Business Plan,Project Appraisal ሊያቀርቡ ይገባል፡፡
	21. ጽ/ቤቱ በብድር የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችን ለታለመለት ዓለማና በታቀደለት ጊዜ እየተከናወነ ስለመሆኑ የክትትል እና የግምገማ ሥራዎች ሊያከናወን ይገባል፡፡
	22. ጽ/ቤቱ የሚሰጠውን ብድር በተመለከተ ባስቀመጠው ያገልግሎት እስታንዳርድ መሠረት ሊሰጥ ይገባል፡፡
III. ጽሕፈት ቤቱ ከፈጻሚ ባለድርሻ አካላት ጋር ቀልጣፋና ወጥ የሆነ የመረጃ አያያዝና	23. የጽ/ቤቱ ከፈንዱ ጋር የተያያዙ የመረጃ አያያዝ፣ አደረጃጀትና የልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡
	24. ጽ/ቤቱ ስለ ወጪን ማስመለስ መርሆ እና የተዘዋዋሪ ፈንድ አጠቃቀም ለተበዳሪዎች እና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ	የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች
ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ	ማስጨበጫ ስራ መስራት አለበት፡፡
	25. .የጽ/ቤቱ የብድር ፍይናንስ ዘመናዊ በሆነና በተጠናከረ የመረጃ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ አስተማማኝና የተቀላጠፈ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡
	26. የጽ/ቤቱን የተለያዩ መረጃዎች ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት (ዌፕ ሳይት) ሊጠቀሙ ይገባል፡፡
	27. የጽ/ቤቱን ስራ በተመለከተ ከተገልጋዮች፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በየሩብ ዓመቱ የውይይት መድረክ ሊዘጋጅና በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

አባሪ 3፡ በናሙና የታዩ ባለድርሻ አካላት እና የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋማት

ተ/ቁ	የተቋማት ስም	የሚገኙበት ክልል
1	የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ	
2	የቡራዩ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት	ኦሮሚያ ክልል
3	የሰበታ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት	ኦሮሚያ ክልል
4	የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግስት የውሃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ	
	የሀዋሳ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት	ደቡብ ክልል
5	የወልቂጤ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት	ደቡብ ክልል
6	የቡታጅራ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት	ደቡብ ክልል
7	የሆሳዕና ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት	ደቡብ ክልል
8	የዱራሜ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት	ደቡብ ክልል
9	የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር	
	የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን	አዲስ አበባ

አባሪ 4፡ ከፋይናንስ ሥራ ሂደት 14/11/2008 እና 25/11/2008 ዓ.ም የተሰጠ ሪፖርት ላይ የፕሮጀክት መዋጮ የተሰብሳቢ ሂሳብ የአመዘጋገብ ልዩነት

ተ/ቁ	ፋይናንስ አድራጊው	ብድር የወሰዱ የከተሞች መጠጥ ውሃና ሳንቴሽን ተቋም ስም	ኮስት ሼሪንግ በቀን 14/11/2008 ከፋይናንስ ስራ ሂደት የተሰጠን ሪፖርት	ኮስት ሼሪንግ በቀን 25/11/2008 ከፋናንስ ስራ ሂደት የተሰጠን ሪፖርት	ልዩነት የቀን 14/11 እና የ25/11/2008	ምርመራ
1	International development assocation	ሆዕሳና	35,478,646.85	44,783,270.00	(9,304,623.15)	የቀን 25/11/2008 ዓ.ም በመብለጥ
2		ቡታጅራ	11,828,779.00	15,844,550.00	(4,015,771.00)	የቀን 25/11/2008 ዓ.ም በመብለጥ
3		ወልቂጤ	18,643,783.20	22,360,000.00	(3,716,216.80)	የቀን 25/11/2008 ዓ.ም በመብለጥ
4		ሰበታ	34,061,260.00	32,975,113.00	1,086,147.00	የቀን 25/11/2008 ዓ.ም በመብለጥ
5		አሶሳ	9,602,855.00	12,845,300.00	(3,242,445.00)	የቀን 25/11/2008 ዓ.ም በመብለጥ
6		ቡራዩ	18,061,437.00	20,620,991.00	(2,559,554.00)	የቀን 25/11/2008 ዓ.ም በመብለጥ

አባሪ 5 ፡ፕሮጀክታቸው ተጠናቀው ያልተሰበሰበ የፕሮጀክት መዋጮ ገንዘብ

ተ/ቁ	ብድር የወሰዱ የከተሞች መጠጥ ውሃና ሳንቴሽን ተቋም ስም	መሰብሰብ ያለበት የፕሮጀክት መዋጮ ድርሻ በቀን 25/11/2008 ከፋናንስ ስራ ሂደት የቀረበ ሪፓርት	በሌጀር የተሰበሰበ የፕሮጀክት መዋጮ ድርሻ	ያልተሰበሰበ የፕሮጀክት መዋጮ	ምርመራ
1	ሆሳዕና	44,783,270.00	37,860,111.85	6,923,158.15	
2	ቡታጅራ	15,844,550.00	13,129,021.00	2,715,529.00	
3	ወልቂጤ	22,360,000.00	18,643,783.27	3,716,216.73	
4	ሰበታ	32,975,113.00	38,096,826.50	(5,121,713.50)	
5	አሶሳ	12,845,300.00	11,200,433.40	1,644,866.60	
6	ቡራዩ	20,620,991.00	22,482,695.00	(1,861,704.00)	

አባሪ 6፡ የብድር ተመላሽ በወቅቱ ያልመለሱ የከተሞች ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ተቋም

ተ.ቁ	የተበዳሪ ተቋማት ሰም	እስካሁን ያልመለሱት	ያልከፈሉበት ዙር	ምርመራ
1	ሚዛን ተፈሪ	816,861.71	2ት ዙር ያልከፈለው	
2	ሐረር	19,474,711.28	የ2ዙር አልከፈለም	
3	አዲስ አበባ	46,389,267.66	የ2ዙር አልከፈለም	
4	አክስም	517,585.63	የ1 ዙር ያልከፈለው	
5	ወልቂጤ	5,081,672.58	የ3ዙር ያልመለሰው	
6	ሆሳዕና	2,076,134.01	የ1 ዙር ያልከፈለው	
7	ቡታጅራ	1,358,265.72	የ2ዙር ያልከፈለው	
8	ጅማ	5,147,576.66	የ1 ዙር ያልከፈለው፡፡	
9	አሶሳ	3,044,638.56	የ3ዙር ያልመለሰው፡፡	
10	ሰበታ	12,717,057.32	የ4ዙር ያልመለሰው፡፡	
11	ቡራዩ	8,629,251.81	የ3ዙር ያልመለሰው፡፡	
12	ሽሬ	1,416,722.94	የ2ዙር ያልመለሰው፡፡	
13	ሊሙገነት	1,385,231.34	የ2ዙር ያልመለሰው፡፡	
14	ሁሩታ	1,143,862.68	የ2ዙር ያልመለሰው፡	
15	ዱራሜ	1,364,781.97	የ2ዙር ያልመለሰው፡	
16	ገንደውሃ	1,390,479.82	የ2ዙር ያልመለሰው፡፡	
	ጠቅላላ ድምር	**111,954,101.69**		

አባሪ 7፡ የብድር ዋስትና የገቡበት ማስረጃ ያልቀረበ ከተሞች ዝርዝር

ተ.ቁ	የከተሞች ስም	የሚገኙበት የክልል ቦታ							
		ኦሮምያ	አማራ	ትግራይ	ደቡብ	ሱማሌ	ቤኒሻንጉል	ጋምቤላ	አዲስ አበባ
1	ሚዛን ተፈሪ				✓				
2	ሀረር	✓							
3	ክብረመንግስት	✓							
4	አክሱም			✓					
5	አዲስ አበባ								✓
6	ሁሩታ	✓							
7	ወልቂጤ				✓				
8	አሶሳ						✓		
9	ወለንጪቲ	✓							
10	ሸኖ	✓							
11	አቦምሳ	✓							
12	ማክሰኝት		✓						
13	ውቅሮ			✓					
14	ቀብሪ ዳሀር					✓			
15	ስሬ	✓							
16	ለገጣፎ	✓							
17	ጎቤሳ	✓							
18	ሃሰሳ	✓							
19	ሰንዳፋ	✓							
20	ወሊሶ	✓							
21	ባሌ ሮቤ	✓							
22	ፊንጫ	✓							
23	ቦዲቲ				✓				

24	ዲላ				✓				
25	ጨንጫ				✓				
26	ሳውላ				✓				
27	ተርጫ				✓				
28	ወራቤ				✓				
29	ሰቆጣ		✓						
30	አቢአዲ			✓					
31	ባንቢስ								
32	ጋቤላ							✓	
33	ያቤሎ	✓							
34	በደኖ				✓				